ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ

መተዳደሪያ ደንብ

(በፓርቲው መስራች ጉባኤ የፀደቀ)

መጋቢት 2011
አዲስ አበባ

ማውጫ

መቅድም 1

ምዕራፍ አንድ፡ ጠቅላላ 2

አንቀጽ 1፡ አጭር ርዕስ 2

አንቀጽ 2፡ የፖርቲው ስያሜ 2

አንቀጽ 3፡ የፓርቲዉ ዋና ጽ/ቤት 2

አንቀጽ 4፡ ድርጅታዊ የአሰራር መርሆች 2

አንቀጽ 5፡ አባልነት 2

አንቀጽ 6፡ የአባልነት መብትና ግዴታ 3

አንቀጽ 7፡ አባልነት የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች 4

ምዕራፍ ሁለት ፡ ድርጅታዊ መዋቅር እና የፓርቲዉ አመራር አካላት 4

አንቀጽ 8፡ የፓርቲው አደረጃጀት እርከን 4

አንቀጽ 9፡ የፓርቲው አመራር አካላት 4

አንቀጽ 10፡ ጠቅላላ ጉባኤ 5

አንቀጽ 11፡ ማዕከላዊ ኮሚቴ 6

አንቀጽ 12፡ የኦዲትና ምርመራ ኮሚሽን 7

አንቀጽ 13፡ የብሄራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ 8

አንቀጽ 14 የክልል ሽንጎ 10

አንቀጽ 15 የክልል ኦዲትና ምርመራ ኮሚቴ 10

አንቀጽ 16 የክልል ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ 11

አንቀፅ 17፡ የዞን/ክፍለ ከተማ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት 12

አንቀፅ 18፡ የወረዳ ሸንጎ 12

አንቀጽ 19፡ የወረዳው ኦዲትና ምርመራ ኮሚቴ 13

አንቀጽ 20፡ የወረዳ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ 13

አንቀጽ 21፡ የቀበሌ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ 14

ምዕራፍ ሦስት፡ የብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ተግባርና ኃላፊነት 15

አንቀጽ 22፡ ሊቀመንበር 15

አንቀጽ 23፡ ምክትል ሊቀመንበርና የምርጫ ጉዳይ ኃላፊ 15

አንቀጽ 24፡ የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ኃላፊ 16

አንቀጽ 25፡ የአባልነትና ድርጅት ጉዳዮች ኃላፊ 16

አንቀጽ 26፡ የውጪ ጉዳይ እና ዲያስፖራ ኃላፊ 17

አንቀጽ 27፡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ኃላፊ 17

አንቀጽ 28፡ የጥናትና ስትራቴጂ ጉዳይ ኃላፊ 18

አንቀጽ 29፡ የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ኃላፊ 18

አንቀጽ 30፡ የሕግ ጉዳዮች ኃላፊ 19
አንቀጽ 31፡ የሴቶች መማክርት ኃላፊ 19
አንቀጽ 32፡ የወጣቶች መማክርት ኃላፊ 20
ምዕራፍ አራት፡ የፓርቲው ልዩ ልዩ አካላት 20
አንቀጽ 33፡ የፓርቲው ጽሕፈት ቤት ኃላፊ 20
አንቀጽ 34፡ የሕዝብ ተመራጮች 21
አንቀጽ 35፡ የአማካሪዎች ሸንጎ 21
ምዕራፍ አምስት፡ ጥፋቶችና ውሳኔ አሰጣጥ 21
አንቀጽ 36፡ የጥፋት አይነቶች 21
አንቀፅ 37፡ የክስ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት 22
አንቀፅ 38፡ የሥነ-ሥርዓት ኮሚቴዎች አወቃቀር 22
አንቀፅ 39፡ የክስ አቀራረብ እና ክስ መስማት ሥነ- ሥርዓት 22
አንቀፅ 40፡ ውሣኔ አሰጣጥ እና የይርጋ ጊዜ 22
አንቀፅ 41፡ ቅጣት 23
አንቀፅ 42፡ ይግባኝ 23
ምዕራፍ ስድስት፡ የፓርቲው የገቢ ምንጭ 23
አንቀጽ 43፡ የፓርቲው የገቢ ምንጮች 23
ምዕራፍ ሰባት፡ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች 24
አንቀጽ 44፡ የፓርቲው የምርጫና የድምጽ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት 24
አንቀጽ 45፡ ስለ ደንብ ማሻሻል እና በደንቡ ውስጥ ስላልተካተቱ ጉዳዮች 24
አንቀጽ 46፡ ስለፓርቲ መፍረስ 24
አንቀጽ 47፡ ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ 24

መቅድም

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ (**ነእፓ**) በሀገራችን አስተማማኝ ሰላምና ዘላቂ ልማት እንዲረጋገጥ፣ የፖለቲካ ስልጣን ከህዝብ ብቻ የሚመነጭበት የፖለቲካ ስርአት እንዲገነባ፣ ዜጎች ሀሳባቸውን በነጻነት የመግለጽ ህጋዊና ተፈጥሯዊ መብታቸው ያለገደብ እንዲከበር፣ የሚዲያና የሲቪል ማህበራት በሀገር ግንባታ ውስጥ ሰፊ ሚና እንዲጫወቱ፣ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች መካከል ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ የመልካም አስተዳደር እንዲጎለብት ኢትዮጵያውያን ለዘመናት ሲያደርጉት የቆዩት ትግል ከዳር እንዲደርስ የበኩሉን አስተዋጾ ለማድረግ የተቋቋመ ሀገራዊ የፖለቲካ ፓርቲ ነው።

ነእፓ የብሄረሰቦች ቋንቋና ባህል በእኩልነት እንዲከበር፣ የሀይማኖት እና የአምልኮ ነጻነትና እኩልነት እንዲረጋገጥ፣ በሀገራችን ፖለቲካዊ ፍትህ እንዲሰፍን፣ የህግ የበላይነት እንዲከበር፣ ለሀገራችን እና ለህዝባችን እድገት **"ነቀርሳ"** ሆኖ ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ እድገቷን በማቀጨጭ ላይ የሚገኘው **ሙሰና** እንዲወገድ፣ ጾታዊ መድሎ እንዲቆምና በተለይም ሴቶች ትምህርትን ጨምሮ የልዩ ልዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል በዋናነት የለዘብተኛ ሊበራል የፖለቲካ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረቱ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በመጠቀም ሀገራችን ካለችበት ውስብስብ ችግሮች ለማላቀቅ ዘመኑ በሚጠይቀው አስተሳሰብ፣ አሰራርና አደረጃጀት የተቋቋመ የፖለቲካ ፓርቲ ነው።

ነእፓ የሀገራችንን ነባራዊና ተጨባጭ የፖለቲካ ሀቆች ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ አህጉራዊና ዓለም ዓቀፋዊ ሂደቶችንና ለውጦችን በጥልቀት በመመዘን፣ የሀገራችንን ጂኦ-ፖለቲካዊ እና ስትራቴጂያዊ መልካም አጋጣሚዎችና ስጋቶች በመተንተን ጠንካራ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመገንባት የሚሰራ የፖለቲካ ፓርቲ ሲሆን የሀገራችንን ውስብስብና የረዥም ጊዜ የፖለቲካ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመፍታት መላውን የኢትዮጵያ ህዝብ ከጎኑ አሰልፎ ለመስራ የሚንቀሳቀስ የፖለቲካ ድርጅት ነው።

ነእፓ ይዞ የተነሳቸውን ራእይ፣ ተልእኮና ዓላማዎች እውን ለማድረግ ብሎም የቀረጻቸውን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፕሮግራሞችና ፖሊሲዎች በተሳካ ሁኔታ መፈጸም እንዲችል ጠንካራ ድርጅታዊ መዋቅር፣ ግልጽ የማስፈጸሚያ ስትራቴጂ እና የአሰራር ስርአት መኖሩ ወሳኝ ነው። ድርጅታዊ አሰራሩን ግልጽ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ሁሉም የፓርቲው አባላትና አመራር አካላት እንዲሁም በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የፓርቲው ልዩ ልዩ የስራ ክፍሎች ኃላፊነታቸውን፣ መብትና ግዴታቸውን በትክክል እንዲረዱና እንዲወጡ ለማስቻል ይህ የመተዳደሪያ ደንብ ተዘጋጅቷል። መተዳደሪያ ደንቡ በፓርቲው ውስጥ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን፣ ውስጠ-ድርጅት ዴሞክራሲዊ አሰራርን ለማዳበር የሚረዳ የፓርቲው ቁልፍ ሰነድ ነው። በሀገራችን የፖለቲካ ስርአት ውስጥ ጠንካራ የዴሞክራሲ ስርአትና ባህል ለመገንባት የሚታገል አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በቅድሚያ በድርጅቱ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ አሰራር ሊያሰፍን ግድ ይሆናል። በዚህ መሰረት ይህ የፓርቲው መተዳደሪ ደንብ የሀገራችንን ህገ-መንግስት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 573/2000፣ ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ህጎችና ደንቦችን እንዲሁም ሳይንሳዊ የአደረጃጀትና የስራ-አመራር መርሆችን ከግምት ውስጥ በማስገባ ተዘጋጅቷል።

መተዳደሪያ ደንቡ የፓርቲው አባላትና አመራር አካላት ውስን የሰው ኃይልን፣ ሀብትን፣ ቴክኖሎጂና ግዜን በመጠቀም ውጤታማ የስራ አፈጻጸም እንዲኖራቸው ለማስቻል፣ በተለያዩ የስራ ክፍሎችና የኃላፊነት እርከኖች መካከል የአስተሳሰብና የአሰራር መስተጋብር እንዲኖር፣ በቅንጅት የመስራት ባህልንና የስራ አካባቢን ለመፍጠር፣ የስልጣንና የስራ መደራረብን ለማስወገድ የሚያስችሉ የአሰራር መርሆችና የአፈጻጸም መመሪያዎችን አካቷል። የፓርቲ አባልነት፣ ደርጅታዊ መዋቅርና የፓርቲው አመራር አካላት፣ የልዩ ልዩ ኮሚቴ አባላት ተግባርና የስራ ኃላፊነት፣ ጥፋቶችና የውሳኔ አሰጣጥ ስርአት፣ የፓርቲው የገቢ ምንጮችና ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የተካተቱ ዋና ዋና ጉዳዮች ናቸው።

ምዕራፍ አንድ፡ ጠቅላላ

አንቀጽ ፩፡ አጭር ርዕስ

ይህ መተዳደሪያ ደንብ የ **"ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

አንቀጽ 2፡ የፓርቲው ስያሜ

የፓርቲው ስያሜ "**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ**" ሲሆን በምህጻረ ቃል "**ነእፓ**" ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

አንቀጽ 3፡ የፓርቲዉ ዋና ጽ/ቤት

የፓርቲው ዋና ጽ/ቤት አዲስ አበባ፣ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 06፣ የቤት ቁጥር 606፣ የክፍል ቁጥር 403 ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች እና በውጭ ሀገር ቅርንጫፎች ወይም የማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች ይኖሩታል፡፡

አንቀጽ 4፡ ድርጅታዊ የአሰራር መርሆች

1. የፓርቲው አባላትና አመራሮች የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ በማክበርና እንዲከበር በማድረግ ውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲን ማስፈን፣
2. በፓርቲ አባላት መካከል በዘር፣ በቋንቋ፣ በአመለካከት፣ በኃይማኖት ወዘተ ምንም ዓይነት ልዩነት እና አድልዎ አለማድረግ፣ በፓርቲው በተለያየ ደረጃ የሚሰጡ ኃላፊነቶች ብቃትን (የትምህርት ደረጃ፣ የስራ ልምድ ወዘተ) መሰረት ያደረጉ እንዲሆኑ ማድረግ፣
3. የፓርቲዉን መሰረታዊ ዓላማዎች፣ የፖሊሲ አቅጣጫዎችና የትግል ስልት በመገንዘብ በተጨባጭ መረጃና በምክንያታዊነት ላይ የተመሰረተ አቋም ማራመድ፣
4. በፓርቲው ውስጥ ሃሳብን በነፃነት የማንሸራሸር መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ለብዙሃን ውሳኔ ተገዥ መሆን፣
5. በፓርቲው የተለያዩ አካላትና አመራር አባላት መካከል ግልጽ የስራ ክፍፍል ማድረግ፣ የክትትልና የቁጥጥር ስልቶችን መዘርጋት፤ በግልጽነትና ተጠያቂነት መርሆች ላይ የተመሰረተ ዲሞክራሲያዊ የአሰራር ባህልን ማዳበር፣
6. የፓርቲውን መዋቅር ጠብቀው የሚተላለፉ የበላይ አካላትን ውሳኔዎችና መመሪያዎችን ማክበርና ተግባራዊ ማድረግ፣
7. ለፓርቲው ታማኝ መሆንና ሚስጥር መጠበቅ

አንቀጽ 5፡ አባልነት

5.1 የአባልነት ቅድመ ሁኔታ

1. ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ፣ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው፣ በፖለቲካ ለመሳተፍ በህግ ገደብ ያልተጣለበት፣
2. የሌላ ፖለቲካ ፓርቲ አባል ያልሆነ፣
3. የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብና ፕሮግራም የሚቀበልና የሚያከብር ብሎም አቅሙ በፈቀደ መጠን ግዴታውን ለመወጣት ዝግጁ የሆነ፣
4. የፓርቲውን ወርኃዊ የገንዘብ መዋጮ ለመክፈልና ሌሎች ግዴታዎችን ለመወጣት ፈቃደኛ የሆነ፡፡

5.2 የአባልነት ጥያቄና የቅበላ ሥነ ስርዓት

1. የፓርቲው አባል ለመሆን ቅድመ ሁኔታዎችን የሚያሟላ እጩ አባል የአባልነት ማመልከቻ ቅጽ አመልካች በቋሚነት በሚኖርበት አካባቢ ቅርብ ለሆነው የፓርቲው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ይሞላል፡፡ አመልካቾች አባል ለመሆን

ሲያመለክቱ ማንነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

2. የአባልነት ጥያቄን የተቀበለው የፓርቲው ቅርንጫፍ ውሳኔውን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለአመልካች ያሳውቃል፡፡ የአባልነት ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘ አመልካች የሙከራ ግዜ አባል በመሆን ይመዘገባል/ትመዘገባለች፡፡ የፓርቲው አባልነት ቁጥር የያዘ መታወቂያ ይዘጋጅለታል/ይዘጋጅላታል፡፡
3. የአባልነት ጥያቄው ተቀባይነት ካላገኘ ውሳኔው ለአመልካች ይገለጻል፡፡ በውሳኔው ቅር የተሰኘ አመልካች በ 1 (አንድ) ወር ጊዜ ውስጥ ለኡዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡ ይግባኝ የተቀበለው አካል በ 1 (አንድ) ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
4. አንድ የፓርቲው አባል የመኖሪያ አድራሻውን ሲቀይር የአባልነት ፋይሉ ወደ አዲሱ አድራሻው ይዘዋወራል፡፡
5. በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የአባልነት ማመልከቻቸውን በሚኖሩበት ሀገር ወይም በቅርብ ለሚገኝ የፓርቲው ቅርንጫፍ ወይም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በማቅረብ አባል መሆን ይችላሉ፡፡

5.3. የዓባልነት ዓይነቶች

1. የፓርቲው አባላት ሙሉ እና የሙከራ ግዜ አባል ናቸው፣
2. ከፓርቲው መስራች ጉባኤ በፊት የተመዘገቡ ሁሉ የፓርቲው ሙሉ አባላት ናቸው፣
3. የፓርቲው የአባልነት ጥያቄው ተቀባይነት ያገኘ አመልካች የአባልነት ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘ ቀን ጀምሮ የሙከራ ግዜ አባል ይሆናል፣
4. በፓርቲው የሙከራ ግዜ አባል ሆኖ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የእጩ አባልነት ግዴታውን በአግባቡ የተወጣ ዕጩ አባል የፓርቲው ሙሉ አባል ይሆናል፣
5. በፓርቲው የብሄራዊ፣ ክልላዊ፣ የዞን/ክፍለ ከተማ እና የወረዳ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች ተጠይቆ አባል ለመሆን ፈቃደኛነቱን የገለፀ ግለሰብ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎቹ ውሳኔ መሰረት በዚህ አንቀጽ ተራ ቁጥር 4 የተጠቀሰውን ጊዜ ሳይጠብቅ የፓርቲው ሙሉ አባል ሊሆን ይችላል፡፡

አንቀጽ 6፡ የአባልነት መብትና ግዴታ

6.1 መብት

ማንኛውም የፓርቲው ሙሉ አባል፡

1. በፓርቲው ስብሳባዎች ላይ ሃሳብ የማቅረብና ድምጽ የመስጠት፣ ሃሳቡን በነጻነት የመግለጽ፣
2. በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ለፓርቲ አባላት ክፍት በሆኑ ኃላፊነቶችና የስራ ቦታዎች የመወዳደር፣ የመምረጥና የመመረጥ፣
3. የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብና ፕሮግራም መከበሩን የመከታተል፣
4. በራስ ተነሳሽነት አዳዲስና ጠቃሚ ሃሳቦችን የማፍለቅ፣ ለፓርቲው አመራር የማስተላለፍ፣
5. በፓርቲው እንቅስቃሴዎችና ተግባራቶች የመሳተፍ፣
6. ድርጅታዊ መዋቅርን ጠብቆ ስለፓርቲው አሰራር ማብራሪያና መረጃ የመጠየቅና ሂስ የማቅረብ፣
7. የፓርቲው አባልነት መታወቂያ ደብተር የማግኘት፣

6.2. ግዴታ

1. የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች ማክበርና የፓርቲውን አመራር ውሳኔዎች ተግባራዊ ማድረግ፣
2. የፓርቲውን ዓላማና ፕሮግራም ማክበርና ተግባራዊ እንዲሆን ማገዝ፣ ለህዝብ ማስተዋወቅና ማሰራጨት፣
3. በተለያዩ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች፣ ፓርቲው በሚጠራቸው የተለዩ ስብሰባዎች መሳተፍ፣

4. የፓርቲውን ዓላማ ከሚጎዱ ማናቸውም እንቅስቃሴዎችና የሥነ-ምግባር ጉድለቶች መቆጠብ፣
5. ለፓርቲው ታማኝ መሆንና ሚስጥር መጠበቅ፣
6. የፓርቲው የሙከራ ግዜ አባል በፓርቲው አመራር ውስጥ ከመምረጥና መመረጥ ውጪ ያሉ የፓርቲው ሙሉ አባላት መብትና ግዴታዎች አሉት/አሏት፣
7. የአባልነት መዋጮን በወቅቱ መክፈልና በፓርቲው የገንዘብ መዋጮ ተግባራት ላይ መሳተፍ፡፡ የአባልነት መዋጮ መጠንና የአከፋፈል ሁኔታ በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ቀርቦ በማዕከላዊ ኮሚቴ ሲጸድቅ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 7፡ አባልነት የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች

1. በራሱ ፍላጎት አባልነቱ እንዲቋረጥ በጽሁፍ ጥያቄ ሲያቀርብ፣
2. በህግ ችሎታ ሲያጣ ወይም በሥነ-ስርዓት ጉዳዮች በፓርቲው የሥነ-ስርአት ኮሚሽን/ኮሚቴዎች ከአባልነት እንዲታገድ ሲወሰን፣
3. የሌላ ፖለቲካ ፓርቲ አባል መሆን፣
4. ጊዜው ማለፉን እያወቀ ለስድስት ተከታታይ ወራት ያለበቂ ምክንያት የአባልነት መዋጮ አለመክፈል፡፡

ምዕራፍ ሁለት ፡ ድርጅታዊ መዋቅር እና የፓርቲዉ አመራር አካላት

አንቀጽ 8፡ የፓርቲው አደረጃጀት እርከን

1. ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ድርጅታዊ መዋቅር በአገር አቀፍ፣ በክልል፣ በዞን/ከፍለ-ከተማ፣ በወረዳ/ከተማ እና ቀበሌ ላይ ይዘረጋል፡፡በተለያዩ አስተዳደራዊ እና የቴክኒክ ምክንያቶች ከላይ የተመለከተው አደረጃጀት ለአሰራር አመቺ በማይሆንባቸው አካባቢዎች እና ሁኔታ፣ የስራ አመቺነትን እና የህዝብ አሰፋፈርን ከግምት ውስጥ በማስገባት አማራጭ አደረጃጀት በብሄራዊ ስራ አስፈጻሚ ተጠንቶ በፓርቲው ማእከላዊ ኮሚቴ ውሳኔ ሊዋቀር ይችላል፣

2. ከዚህ በተጨማሪ ፓርቲው የሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ፣ እንዲሁም በየደረጃው የፌደራል፣ የክልል፣ የዞን/ከፍለ-ከተማ፣ የወረዳና ቀበሌ ምክር ቤቶች የህዝብ ተወካዮች ቡድን ይኖሩታል፡፡

አንቀጽ 9፡ የፓርቲው አመራር አካላት

ፓርቲው የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡፡

1. አገር አቀፍ

1. ጠቅላላ ጉባኤ
2. ማዕከላዊ ኮሚቴ
3. ብሄራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ
4. የኦዲትና ምርመራ ኮሚሽን

2. ክልል

1. የክልል ሸንጎ
2. የክልል ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ
3. የክልል የኦዲትና ምርመራ ኮሚቴ

3. ዞን/ከፍለ ከተማ

1. የዞን ምክር ቤት
2. የዞን ስራ አስፈጻሚ

4. **ወረዳ/ከተማ**
    1. የወረዳ/ከተማ ሸንጎ
    2. የወረዳ/ከተማ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ
    3. የወረዳ/ከተማ የኦዲትና ምርመራ ኮሚቴ
5. **የቀበሌ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ**
6. **ልዩ ልዩ አካላት**
    1. የወጣቶች መማክርት
    2. የሴቶች መማክርት
    3. የፌደራል፣ የክልል፣ የዞን/ከፍለ-ከተማ፣ የወረዳ እና ቀበሌ ህዝብ ተወካዮች/ተመራጮች ቡድን
    4. እንደ አስፈላጊነቱ በፓርቲው የተለያዩ አካላት የሚቋቋሙ ግዜያዊ ወይም ቋሚ ኮሚቴዎች

አንቀጽ 10፡ ጠቅላላ ጉባኤ

10.1. የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤው 150 አባላት የሚኖሩት ሲሆን የሚከተሉትን የፓርቲው አካላት ይይዛል

1. የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ቋሚና ተለዋጭ አባላት፤ የኦዲትና ምርመራ ኮሚሽን አባላት እና የብሄራዊ ሥራ እስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት፣
2. ከሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች የህዝብ ብዛትን፣ የክልሎችን የእድገት ደረጃ፣ የህዝብ ድጋፍ ወዘተ ታሳቢ ባደረገ ሁኔታ የሚወከሉ አባላት፣
3. በተለያየ መንገድ ለፓርቲው የጎላ አስተዋጽኦ ካደረጉና ለጠቅላላ ጉባኤ አባልነት የሚያበቃ ውክልና ካላገኙ አባላት መካከል በማዕከላዊ ኮሚቴ የሚመረጡ የፓርቲው አባላት፣
4. የወጣቶች እና ሴቶች መማክርት ተወካዮች::

10.2 የጠቅላላ ጉባኤው ሥልጣንና ተግባር

የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ የፓርቲው ከፍተኛ የስልጣን አካል ሲሆን የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1. የፓርቲውን ሊቀመንበር፣ የማዕከላዊ ኮሚቴ እና የኦዲትና ምርመራ ኮሚሽን አባላትን ይመርጣል፤ ይሸራል፤
2. የፓርቲውን ፕሮግራም እና የመተዳደሪያ ደንብ ያፀድቃል፣ ያሻሽላል፣
3. የፓርቲውን ስያሜ፣ አርማ፣ ሰንደቅ ዓላማ፣ ያጸድቃል፣
4. ከማዕከላዊ ኮሚቴ እና ከኦዲትና ምርመራ ኮሚሽን የሚቀርቡለትን የሥራ ክንውን ሪፖርቶች መርምሮ በሙሉ ወይም ከማሻሻያ ሀሳብ ጋር ያጸድቃል፣
5. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን፣ የማዕከላዊ ኮሚቴና የኦዲትና ምርመራ ኮሚሽን የስራ አፈጻጸም ይገመግማል፣
6. ፓርቲው ከሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር የሚያደርገውን መቀናጀት፣ ግንባር መፍጠርና መዋሀድ አስመልክቶ ውሳኔ ይሰጣል፣
7. ፓርቲውን በሚመለከቱ በማናቸውም ሌሎች ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ይሰጣል፣
8. የጠቅላላ ጉባኤ አባላት የስራ ዘመን አራት ዓመት ሲሆን በተከታታይ ለሁለት ጊዜ ሊያገለግሉ ይችላሉ::

10.3 የጠቅላላ ጉባኤ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባ

መደበኛ ስብሰባ

1. የጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ በየሁለት ዓመቱ ይካሄዳል፣
2. የጠቅላላ ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ ጥሪ የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ያደርጋል፣ የጉባኤውን አጀንዳም ያዘጋጃል፣

3. የጠቅላላ ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ ጥሪ ከስብሰባው ፲0 ቀን በፊት ለአባላት ሊደርስ በሚችል የጥሪ መንገድ (በጋዜጣ፣ አጭር የጽሁፍ መልእክት፣ በፓርቲው ኦፊሴላዊ ኢ-ሜይል፣ ማህበራዊ ሚዲያ ገጽ እና ድረ-ገጽ ወዘተ) በአንዱ ወይም በሁሉም መንገድ ጥሪ ይተላለፋል፣
4. መደበኛ ጉባኤውን ለመጥራት ከአቅም ባላይ የሆነ ምክንያት ሲያጋጥም ማዕከላዊ ኮሚቴው የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባ እስከ 6 ወራት ሊያራዝም ይችላል፡፡

አስቸኳይ ስብሰባ

1. የጠቅላላ ጉባኤ አስቸኳይ ስብሰባ ጥሪ በፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ አማካኝነት ይካሄዳል፡፡ አስቸኳይ ስብሳባ በሌሎች የፓርቲው አካላት ማለትም የፓርቲው ሊቀመንበር ወይም የኡዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን ወይም ከጉባኤው አባላት ፣/3 በጽሁፍ ሲጠይቁ በማዕከላዊ ኮሚቴው አማካኝነት የአስቸኳይ ስብሰባ ጥሪ ይካሄዳል፡፡
2. የጠቅላላ ጉባኤ አስቸኳይ ስብሰባ አጀንዳ/ዎች/ አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ በጠየቀው አካል ቀርበው በማዕከላዊ ኮሚቴ ተቀባይነት ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ በአስቸኳይ ስብሰባ ላይ በቅድሚያ ከተወሰኑት አጀንዳዎች ውጪ ሌላ አጀንዳ አይስተናገድም፣
3. የጠቅላላ ጉባኤ አስቸኳይ ስብሰባ ለማካሄድ ከላይ የተገለጹት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ፣ የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ፣ (አንድ) ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል፣
4. የጠቅላላ ጉባኤው መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ማዕከላዊ ኮሚቴው በሚወስነው ቦታ ይካሄዳል፡፡

አንቀጽ ፲፣ ማዕከላዊ ኮሚቴ

፲.፣ አደረጃጀትና አሰራር

ማዕከላዊ ኮሚቴው ከጠቅላላ ጉባኤው ቀጥሎ ከፍተኛ የፓርቲው ውሳኔ ሰጭ አካል ሲሆን በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጡ 35 ሙሉና 15 ተለዋጭ አባላት ይኖሩታል፣

1. ማዕከላዊ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ሲሆን የሥራ ክንውን ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል፣
2. የማዕከላዊ ኮሚቴው መደበኛ ስብሰባ በየሶስት ወሩ የሚካሄድ ሲሆን በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ጥያቄ ወይም የማዕከላዊ ኮሚቴው ፣/3ኛው አባላት ሲጠይቁ የማዕከላዊ ኮሚቴው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፣
3. የማዕከላዊ ኮሚቴው ሰብሳቢ በየሶስት ወሩ በሚካሄደው ስብሰባ ይመረጣል፣ የፓርቲው ጽ/ቤት ኃላፊ የማእከላዊ ኮሚቴው ፀኃፊ ሆኖ ያገለግላል፣
4. ማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ሲያካሂድ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና የኡዲትና ምርመራ ኮሚሽን አባላት ይሳተፋሉ፣
5. የማዕከላዊ ኮሚቴ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ማዕከላዊ ኮሚቴው በሚወስነው ቦታና ጊዜ ይካሄዳሉ፣
6. የማዕከላዊ ኮሚቴው አባላት በአመት ውስጥ በሁለት መደበኛ ስብሰባ ያለበቂ ምክንያት ሳይገኙ ከቀሩ ወይም የዲሲፕሊን ጉድለት መፈፀማቸው በኡዲትና ምርመራ ኮሚሽን ሲረጋገጥ እና በጠቅላላ ጉባኤው ሲጸድቅ ከምክር ቤት አባልነታቸው ይወጣሉ፡፡ የማእከላዊ ኮሚቴው ሰብሳቢ ተለዋጭ አባላት ባላቸው የድምጽ ቅደም ተከተል መሰረት እነሱን ተክተው እንዲሰሩ ጥሪ ያደርጋል፣
7. ለማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነት ምርጫ እጩ አባላት በሚከተሉት መንገዶች ሊቀርቡ ይችላሉ፣
    1. በቅድሚያ ከጠቅላላ ጉባኤ አባላት ውስጥ ራሳቸውን እጩ አድርገው ሊያቀርቡ ይችላሉ
    2. በመቀጠል በጠቅላላ ጉባኤ አባላት ጥቆማ ይካሄዳል፣
    3. ፓርቲው ሲመሰረት በመስራች አባላት መካከል ጠንካራ ትውውቅ ባለመኖሩ ሊፈጠር የሚችለውን የመረጃ ክፍተት ለመሙላት በፓርቲው መስራች ጉባኤ ላይ እጩ የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ጥቆማ በፓርቲው አደራጅ ኮሚቴ ሊደረግ ይችላል፣
8. ዕጩ አባላት ራሳቸው ወይም የጠቆማቸው አባል ስለ እጩ አባሉ አጭር መረጃ እንዲሰጡ ይደረጋል፣

9. የማዕከላዊ ኮሚቴው የሙያ፣ የአካባቢ፣ የጾታ ወዘተ ተዋጽዖን በጠበቀ መልኩ ይዋቀራል፣
10. የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን አራት አመት ሲሆን ለሁለት ተከታታይ የስራ ዘመን ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

11.2 የማዕከላዊ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር

1. የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ፣ ፕሮግራምና ሌሎች የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔዎችን ይፈጽማል ወይም እንዲፈጸሙ ያደርጋል፣ የጠቅላላ ጉባኤውን ውሳኔ መሰረት አድርጎ ልዩ ልዩ የአፈፃፀም መመሪያዎችንና ደንቦችን ያወጣል ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣
2. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን ስራ ይከታተላል፣ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚቀርብለትን የስራ ዕቅድና በጀት መርምሮ ያጸድቃል፣ ያፀደቀውን በጀት በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፣
3. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ ዓርማ፣ ሰንደቅ ዓላማና መዝሙር እንዲሻሻል በማድረግ ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ እንዲጸድቅ ያደርጋል፣
4. ፓርቲውን በመወከል በየደረጃው በምርጫ የሚወዳደሩ አባላት ዝርዝር በስራ አስፈጻሚው ተዘጋጅቶ ሲቀርብ መርምሮ ያፀድቃል፣
5. የፓርቲውን የክልል ቅርንጫፎች ለመክፈት በስራ አስፈጻሚ የሚቀርብለትን ጥያቄ መርምሮ ያጸድቃል፣
6. ከጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

አንቀጽ 12፡ የኦዲትና ምርመራ ኮሚሽን

ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ አምስት አባላት ያሉት የኦዲትና ምርመራ ኮሚሽን በጠቅላላ ጉባኤ ይቋቋማል፡፡ ኮሚሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ ይተረጉማል፣ በፓርቲው የሚወጡ መመሪያዎች ከመተዳደሪያ ደንቡ እና ከፓርቲው ፕሮግራም ጋር መጣጣማቸውን ያረጋግጣል፣
2. የፓርቲው ገንዘብና ንብረት በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ዘመናዊ የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ስርአት እንዲዘረጋ ድጋፍ ያደርጋል፣ የስራ አስፈፃሚውን ሪፖርቶች በመመርመር፣ አስተያየትና የማሻሻያ ሀሰቦች ካሉ ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና ለማዕከላዊ ኮሚቴው ያቀርባል፣
3. በፓርቲው ውስጥ የሚከሰቱ የአባላትም ሆነ የአመራር አካላት የሥነ-ሥርዓት ጉዳዮችን የሚያይ የሥነ-ሥርዓት ኮሚቴ ያቋቁማል፣ በሥነ-ሥርዓት ኮሚቴ የተሰጡ ውሳኔዎችን ይግባኝ ይመረምራል ውሳኔም ይሰጣል፣ በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ የፓርቲው አመራር አባላትን በተመለከተ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያስወስናል፣
4. ከአባላት የሚቀርቡ ቅሬታዎችንና ጥቆማዎችን መሰረት በማድረግ የአሰራር ጉድለቶች በወቅቱ እንዲታረሙና ችግሮችም እንዲፈቱ የምክርና የሙያ ድጋፍ ያደርጋል፣
5. በፓርቲው ድርጅታዊ መዋቅር ውስጥ በየትኛውም ደረጃ የአሰራር ግድፈት፣ የደንብና መመሪያ ጥሰት አለ ብሎ ሲያምን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይወያያል፣ አስፈላጊው ማስተካካያ እንዲደረግ ለሚመለከተው አካል በቃልና በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡ ችግሮቹ የማይታረሙ እና የፓርቲው ህልውና አደጋ ውስጥ ይወድቃል ብሎ ሲያምን በጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ወይም እንደ ጉዳዩ ክብደትና ውሳኔው ከሚፈልገው ጊዜ አንጻር የጠቅላላ ጉባኤ አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራና በታዩት ችግሮች ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ ያደርጋል፣
6. የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን አባላት ምርጫ እጩ አባላት በሚከተሉት መንገዶች ሊቀርቡ ይችላሉ፣
    1. በጠቅላላ ጉባኤ አባላት ጥቆማ ይካሄዳል፣

2. ፓርቲው ሲመሰረት በመስራች አባላት መካከል ጠንካራ ትውውቅ ባለመኖሩ ሊፈጠር የሚችለውን የመረጃ ክፍተት ለመሙላት በፓርቲው መስራች ጉባኤ ላይ እጩ የኡዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ጥቆማ በፓርቲው አደራጅ ኮሚቴ ሊደረግ ይችላል፣

7. ዕጩ አባላት ራሳቸው ወይም የጠቆማቸው አባል ስለ እጩ አባሉ አጭር መረጃ እንዲሰጡ ይደረጋል፣
8. የኡዲትና ምርመራ ኮሚሽን ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ከመካከሉ ይመርጣል፣ የፓርቲው ጽ/ቤት ኃላፊ የኮሚሽኑ ፀኃፊ ሆኖ ይሰራል፣ ኮሚሽኑ የራሱን ውስጣዊ የአሰራር ሥነ-ሥርዓት ያዘጋጃል፣
9. በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፣
10. የኡዲትና ምርመራ ኮሚሽን አባላት የስራ ዘመን አራት አመት ሲሆን በተከታታይ ለሁለት የስራ ዘመን ሊያገለግሉ ይችላሉ::

አንቀጽ 13፡ የብሄራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

13.1 የብሄራዊ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አመሰራረትና አሰራር

1. የፓርቲው ብሄራዊ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በፓርቲው ሊቀመንበር አማካኝነት ከማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ውስጥ ተመርጠው በማዕከላዊ ኮሚቴው ተቀባይነት የሚያገኙ አባላትን ይይዛል፣ ተጠሪነታቸው ለሊቀመንበሩ ይሆናል፣
2. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ፲፩ ቋሚ እና 3 ተጠባባቂ አባላት ይኖሩታል፣ ተጠባባቂ የስራ አስፈጻሚ አባላት በሚያገኙት ድምጽ መሰረት ቋሚ አባል ይሆናሉ፣
3. ከማእከላዊ ኮሚቴው አባላት መካከል ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚመረጡት የማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነታቸው አይነሳም፣ በማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይም በአባልነታቸው ይሳተፋሉ፣ ድምጽ ይሰጣሉ፣
4. ለብሄራዊ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት የተመረጡ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት በምትካቸው ባላቸው ድምጽ መሰረት ተጠባባቂ የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት የኮሚቴው ሙሉ አባል ይሆናሉ፣
5. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አባላት በመካከላቸው የስራ ድልድል ያደርጋሉ፣
6. የብሄራዊ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለፓርቲው ማእከላዊ ኮሚቴ ይሆናል፣
7. የብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ መደበኛ ስብሳበ በሁለት በሳምንት አንድ ጊዜ የሚካሄድ ሲሆን በሊቀመንበሩ ወይም በኮሚቴው 1/3 አባላት ጥያቄ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል፣
8. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን አራት አመት ሲሆን በተከታታይ ለሁለት ጊዜ ማገልገል ይችላሉ::

13.2 የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት

1. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚከተሉትን የስራ ኃላፊዎች ያካትታል፣
    1. ሊቀመንበር
    2. ምክትል ሊቀመንበርና የምርጫ ጉዳይ ኃላፊ
    3. የአባልነትና አደረጃጀት ጉዳይ ኃላፊ
    4. የኮሚኒኬሽን ጉዳይ ኃላፊ
    5. የውጭ ግንኙነት እና ዲያስፖራ ኃላፊ
    6. ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ኃላፊ
    7. የጥናትና ስትራቴጂ ጉዳይ ኃላፊ
    8. የህግ ጉዳዮች ኃላፊ
    9. የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ኃላፊ
    10. የወጣቶች መማክርት ሰብሳቢ
    11. የሴቶች መማክርት ሰብሳቢ

2. ከላይ በተመለከቱት የስራ አስፈጻሚ ኃላፊዎች ሰብሳቢነት የሚሰሩ ቋሚ እና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውሳኔ ይቋቋማሉ፣ የኮሚቴዎቹ አባላት ብዛት እንደ ኮሚቴዎቹ የስራ ባህሪ ሊለያይ ይችላል፣
3. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከላይ ለተመለከቱት የስራ አስፈጻሚ የስራ ክፍሎች ቋሚ እና ግዜያዊ ሰራተኞችና ባለሙያዎች በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ውሳኔ ሊመደቡ ይችላሉ::

13.3፣ የብሄራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስልጣንና ኃላፊነት

የብሄራዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚከተሉት ስልጣንና ኃላፊነቶች አሉት፣

1. የጠቅላላ ጉባኤ እና የማዕከላዊ ኮሚቴውን ውሳኔዎችና መመሪያዎች በስራ ላይ ያውላል፣ የስራ እንቅስቃሴውን በተመለከተ በየሶስት ወሩ ለማዕከላዊ ኮሚቴው እና ለኡዲትና ምርመራ ኮሚሽን ሪፖርት ያቀርባል፣
2. የፓርቲውን ዓመታዊ የስራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፤ በማዕከላዊ ኮሚቴው ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣
3. የስራ አስፈጻሚውን ልዩ ልዩ የስራ ክፍሎች የስራ አፈጻጸም ይገመግማል፣
4. ከፓርቲው አባላት መካከል በሊቀመንበሩ ተመርጦ ለፓርቲው ጽሕፈት ቤት ኃላፊነት የቀረበለትን እጩ ብቃት መርምሮ ያፀድቃል፣
5. ፓርቲውን በመወከል በየደረጃው በምርጫ የሚወዳደሩ አባላት ዝርዝር አሰናድቶ ለማዕከላዊ ኮሚቴ ያቀርባል፣ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣
6. የፓርቲውን ክልላዊ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ለማቋቋም በጥናት ላይ የተመሰረተ ጥያቄ ለማዕከላዊ ኮሚቴው ያቀርባል፣ ሲያጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣ የፓርቲው የክልል ሊቀመንበር በክልሉ ሸንጎ እስኪመደብ ድረስ ግዚያዊ አስተባባሪ ይሰይማል፣
7. ለፓርቲው የክልል ጽ/ቤቶችና ልዩ ልዩ የስራ ክፍሎች አስፈላጊውን የሙያ ድጋፍና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በክልሎች እየተዘዋወረ የስራ አፈጻጸማቸውን በአካል ተገኝቶ ይገመግማል፣
8. ፓርቲው በራሱ ወይም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ሊተገብራቸው የሚችሉ የፕሮጀክት ሀሳብ ይነድፋል፣ ዝርዝር የፕሮጀክት ሰነድ ያዘጋጃል/እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ የገንዘብና ሌሎች የፕሮጀክት ግብአቶች ሲሟሉ ተግባራዊ ያደርጋል፣
9. እንደ ሁኔታው ለፓርቲው ስራ የሚያስፈልጉ ጊዜያዊ ግብረ ኃይሎችን ወይም ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ በፓርቲው መዋቅር ውስጥ የሚያስፈልጉ ቋሚ አደረጃጀቶችን አጥንቶ በማዕከላዊ ኮሚቴ ሲጸድቅ ተግባራዊ ደርጋል፣
10. በብሄራዊ እና በክልል ደረጃ ከተቋቋሙ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበራሰብ ድርጅቶች፣ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ እና ከግል ዘርፍ ጋር በጋራ አጀንዳ ላይ ለመስራት የሚያስችሉ አሰራሮችን ይቀይሳል፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራ ከሚገኙ እና ከፓርቲው ጋር ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ርዕዮተ ዓለም፣ ዓላማ እና ፕሮግራም ካላቸው አካላት ጋር በጋራ ለመስራት የሚያችሉ የጋራ መድረኮችን ለመፍጠር ጥናት ያደርጋል፣ ይተገብራል፣
11. ሀገራዊ፣ አካባቢያዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም ዓቀፋዊ የፖለቲካ፣ ማህበራዊና፣ኢኮኖሚያዊ፣ ስትራቴጂያዊ፣ የጸጥታና ደህንነት ሂደቶችን በጥልቀት በመመርመር፣ በየደረጃው ለሚገኙ የፓርቲው አመራና አካላት ያሳውቃል፣
12. የክልል፣ የወረዳና የቀበሌ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን እንዲሁም የክፍለ-ከተማ/ዞን አስተባባሪዎችን ሥልጣንና የስራ መዘርዝር ያዘጋጃል፤ በማዕከላዊ ኮሚቴ ሲፀድቅ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣
13. ከማዕከላዊ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

አንቀጽ 14 የክልል ሸንጎ

1. የክልል ሸንጎዎች ተጠሪነታቸው ለፓርቲው ማእከላዊ ኮሚቴ ሲሆን በክልል ደረጃ የፓርቲው ከፍተኛ የስልጣን አካል ነው፣
2. የፓርቲውን የክልል ሊቀመንበር፣ የክልሉን የኡዲትና ምርመራ ኮሚቴ አባላት ይመርጣል፤ ይሽራል፣ ከክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና ከኡዲትና ምርመራ ኮሚቴ የሚቀርቡለትን የሥራ ክንውን ሪፖርቶች መርምሮ በሙሉ ወይም ከማሻሻያ ሀሳብ ጋር ያጸድቃል፣
3. የክልል ሸንጎዎች የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ ፖሊሲዎችና ህጎች እንዲሁም የክልላቸውን ታሪካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ ለትግበራ ምቹ የአፈጻጸም መመሪያ እና ደንብ፣ ክልላዊ የምርጫ ማኒፌስቶ፣ የምርጫ ቅስቀሳ ስትራቴጂ ወዘተ ሊያዘጋጁ ይችላሉ፣
4. በክልሉ ሊቀመንበር አማካኝነት የሚቀርቡትን የክልሉን የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እጩ አባላት ተመልክቶ ያጸድቃል፣ ይሽራል፣
5. የክልል ሸንጎ አባላት የሚከተሉትን ያካትታል፤ የክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፣ የክልሉ የኡዲትና ምርመራ ኮሚቴ አባላት፣ የወረዳ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሳቢና ም/ሰብሳቢ፣ በክልሉ ውስጥ በተለያየ መንገድ ለፓርቲው የጎላ አስተዋጽኦ ካደረጉና ለክልሉ ሸንጎ አባልነት የሚያበቃ ውክልና ከሌላቸው አባላት መካከል በክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚመረጡ የፓርቲው አባላት፣
6. የክልል ሸንጎ መደበኛ ስብሰባ በየዓመቱ የሚካሄድ ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፣
7. የክልሉ ሸንጎ መደበኛ ስብሰባ ጥሪ የክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያደርጋል፣ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴን ያቋቁማል፣ የጉባኤውን አጀንዳ ያዘጋጃል፣ የክልሉን መደበኛ ጉባኤ ለመጥራት ከአቅም ባላይ የሆነ ምክንያት ሲያጋጥም የክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከፓርቲው ሊቀመንበር ጋር በመወያየት የክልሉን ሸንጎ ስብሰባ እስከ 3 ወራት ሊያራዝም ይችላል፣ የክልሉ ሸንጎ መደበኛ ስብሰባ የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ ከመካሄዱ በፊት ይካሄዳል፣
8. የክልል ሸንጎ መደበኛ ስብሰባ ጥሪ ከስብሰባው በፊት ቢያንስ አንድ ሳምንት ቀድሞ ለአባላት ሊደርስ በሚችል የጥሪ መንገድ (በጋዜጣ፣ አጭር የሞባይል መልእክት፣ ኢ-ሜይል፣ ማህበራዊ ሚዲያ፣ የፓርቲው ኦፊሴላዊ ድረ-ገጽ ወዘተ) በአንዱ ወይም በሁሉም መንገድ ጥሪ ይተላለፋል፣
9. የክልል ሸንጎ አስቸኳይ ስብሰባ በፓርቲው የክልል ሊቀመንበር ወይም በኡዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ወይም ከክልሉ ሸንጎ አባላት 1/3 በጽሁፍ ሲጠይቁ የክልሉ ሊቀመንበር ከፓርቲው ሊቀመንበር ጋር በመነጋገር ጥሪ ይካሄዳል፣ የክልል ሸንጎ አስቸኳይ ስብሰባ አጀንዳ/ዎች/ አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ በጠየቀው አካል ይቀርባሉ፣ በአስቸኳይ ስብሰባ ላይ በቅድሚያ ከተወሰኑት አጀንዳዎች ውጪ ሌላ አጀንዳ አይስተናገድም፣
10. የክልል ሸንጎ አባላት የስራ ዘመን አራት አመት ሲሆን በተከታታይ ለሁለት ጊዜ ሊያገለግሉ ይችላሉ::

አንቀጽ 15 የክልል ኡዲትና ምርመራ ኮሚቴ

አምስት አባላት ያሉት የኡዲትና ምርመራ ኮሚቴ በክልሉ ሸንጎ ይቋቋማል:: ተጠሪነቱም ለክልሉ ሸንጎ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል::

1. በክልል ደረጃ የፓርቲው ገንዘብና ንብረት በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ዘመናዊ የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ስርአት እንዲዘረጋ ድጋፍ ያደርጋል፣ የክልሉን የስራ አስፈፃሚ ሪፖርቶች በመመርመር፣ አስተያየትና የማሻሻያ ሀሰቦች ካሉ ለክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና ለክልሉ ሸንጎ ያቀርባል፣
2. በክልሉ ውስጥ የሚከሰቱ የአባላትም ሆነ የአመራር አካላት የሥነ ሥርዓት ጉዳዮችን የሚያይ የሥነ-ሥርዓት ኮሚቴ ያቋቁማል፣ በስነ-ስርዓት ኮሚቴ የተሰጡ ውሳኔዎችን ይግባኝ ይመረምራል የመጨረሻ ውሳኔም ይሰጣል፣ ከክልሉ

የፓርቲው አባላት የሚቀርቡ ቅሬታዎችንና ጥቆማዎችን መሰረት በማድረግ የአሰራር ጉድለቶች በወቅቱ እንዲታረሙና ችግሮችም እንዲፈቱ የምክርና የሙያ ድጋፍ ያደርጋል፣

3. በፓርቲው ክልላዊ መዋቅር ውስጥ በየትኛውም ደረጃ የአሰራር ግድፈት፣ የደንብና መመሪያ ጥሰት አለ ብሎ ሲያምን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይወያያል፣ አስፈላጊው ማስተካካያ እንዲደረግ ለሚመለከተው አካል በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡ ችግሮቹ የማይታረሙ እና የፓርቲው አሰራርና እንቅስቃሴ አደጋ ውስጥ ይወድቃል ብሎ ሲያምን የክልሉ ሸንጎ መደበኛ ስብሰባ ወይም እንደ ጉዳዩ ክብደትና ውሳኔው ከሚፈልገው ጊዜ አንጻር አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራና በታዩት ችግሮች ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ ያደርጋል፣
4. የክልሉ የኡዲትና ምርመራ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ጸኃፊ ይኖሩታል፣ እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች የስራ ድልድል ያደርጋል፣ ከብሄራዊ የኡዲትና ምርመራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር የራሱን የስራ መመሪያ በማዘጋጀት በክልሉ ሸንጎ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣
5. ከብሄራዊ ኡዲትና ምርመራ ኮሚሽን ጋር ጠንካራ የስራ ግንኙነት ይፈጥራል፣ ስራውን በውይይትና በቅንጅት ይሰራል፣
6. በክልሉ ሸንጎ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፣
7. የክልሉ የኡዲትና ምርመራ ኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን አራት አመት ሲሆን በተከታታይ ለሁለት የስራ ዘመን ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

አንቀጽ 16 የክልል ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

16.1 የክልል ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስልጣንና ኃላፊነት

የክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለክልሉ ሸንጎ ሲሆን የሚከተሉት ስልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፣

1. የክልሉን የስራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል በክልሉ ሸንጎ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣ የክልሉን ሸንጎ ውሳኔዎችና መመሪያዎች በስራ ላይ ያውላል፣ የፓርቲውን ክልላዊ የስራ እንቅስቃሴ ለክልሉ ሸንጎ እና ለክልሉ የኡዲትና ምርመራ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፣
2. በክልሉ ሊቀመንበር ከክልሉ የፓርቲው አባላት መካከል ተመርጦ ለፓርቲው የክልል ጽ/ቤት ኃላፊነት የቀረበለትን እጩ ብቃት መርምሮ ያፀድቃል፤ ይሸራል፣
3. ፓርቲውን በመወከል በክልል፣ በዞን/ከፍለ-ከተማ፣ በወረዳ፣ በቀበሌና በተለያዩ ደረጃዎች ለምርጫ የሚወዳደሩ አባላት ዝርዝር አዘጋጅቶ ለብሄራዊ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣
4. በክልል ደረጃ እንደ ሁኔታው ለፓርቲው ስራ የሚያስፈልጉ ጊዜያዊ ግብረ-ኃይሎችን ወይም ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ በክልሉ ውስጥ የፖለቲካ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ደህንነት ሂደቶችንና ለውጦችን በመከታተል ለብሄራዊ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና በክልሉ በየደረጃው ለሚገኙ የፓርቲው አባላትና አካላት ያሳውቃል፣
5. በክልሉ ውስጥ ከሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበራሰብ ድርጅቶች፣ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ የግል ዘርፍ እንዲሁም ከፓርቲው ጋር ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ርዕዮተ ዓለም፣ ዓላማ እና ፕሮግራም ካላቸው አካላት ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችሉ አሰራሮችን አጥንቶ ለብሄራዊ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣
6. ለብሄራዊ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ መደበኛ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ያቀርባል፣ ከብሄራዊ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና ከሌሎች የፓርቲው ብሄራዊ አካላት ጋር በአላማና በተግባር አንድነት መርህ ይሰራል፣
7. በክልሉ ሸንጎ እና በብሄራዊ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፣
8. የክልሉ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን አራት አመት ሲሆን በተከታታይ ለሁለት ጊዜ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

16.2 የክልል ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት

የክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት

1. የክልል ሊቀመንበር
2. ምክትል ሊቀመንበር
3. የኮሚኒኬሽን ጉዳይ ኃላፊ
4. የአባልነትና አደረጃጀት ጉዳይ ኃላፊ
5. የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ኃላፊ
6. የሴቶች መማክርት ኃላፊ
7. የወጣቶች መማክርት ኃላፊ

አንቀፅ 17፡ የዞን/ክፍለ ከተማ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

የፓርቲው የዞን/ክፍለ ከተማ ማተባባሪያ ጽ/ቤት በክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚደራጅ ሲሆን ተጠሪነቱም ለክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይሆናል፡፡ የዞን/ክፍለ ከተማ ማስተባባሪያ ጽ/ቤቶች የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች አላቸው፣

1. በዞኑ/በክፍለ ከተማው የሚገኙ ወረዳዎችን ያስተባብራል፣ የቴክሊክ ድጋፍ ይሰጣል፣ ስራዎቻቸውን ይከታተላል፣
2. ወረዳዎችን በማስተባበር ፓርቲውን በተመለከተ በዞኑ/ክፍለ ከተማ ውስጥ የሚደረጉ ስራዎችን ያቀናጃል፣
3. ከፓርቲው የክልል አካላት የሚተላለፉ መመሪያዎችን ለወረዳዎች እንዲደርስ እንዲሁም ከዞኑ የመወሰን አቅም በላይ የሆኑ የወረዳ ጉዳዮችን ለክልል አካላት በማድረስ ውሳኔ እንዲሰጥ ያደርጋል፣
4. የፓርቲውን የወረዳ አካላት አቅም በስልጠናና በሌሎች መንገዶች እንዲገነባ ያደርጋል፣ በዞኑ/ክፍለ ከተማ ውስጥ ባሉ የፓርቲው የወረዳ አካላት መካከል ጠንካራ ድርጅታዊ ግንኙነት እንዲፈጠር እገዛ ደርጋል፣
5. የዞኑ/ክፍለ ከተማ አስተባባሪዎች አወቃቀር ዝርዝር መመሪያ በብሄራዊ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተዘጋጅቶ በማእከላዊ ኮሚቴ ሲጸድቅ ተግባራዊ ይነል፣
6. የዞኑ/ክፍለ ከተማ አስተባባሪዎች የስራ ዘመን አራት ዓመት ሲሆን በተከታታይ ለሁለት ጊዜ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

አንቀፅ 18፡ የወረዳ ሸንጎ

18.1. የወረዳ ሸንጎ አመሰራረትና አሰራር

1. የወረዳው ሸንጎ አባላት የወረዳው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት፣ የወረዳው ኡዲትና ምርመራ ኮሚቴ አባላት፣ በወረዳው ውስጥ ያሉ የቀበሌ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች ሰብሳቢዎች፣
2. የወረዳ ሸንጎ ሊቀ መንበርና እና ምክትል ሊቀ መንበር ይኖረዋል፣
3. የወረዳ ሸንጎ መደበኛ ስብሰባ በየአመቱ ይሆናል፤ ሆኖም በፓርቲው የወረዳ ሊቀመንበር ጥያቄ የሸንጎው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፣ የወረዳ ሸንጎ መደበኛ ስብሰባውን የክልል ሸንጎ መደበኛ ስብሰባ ከመደረጉ በፊት ያካሂዳል፣
4. የወረዳ ሸንጎ አባላት የስራ ዘመን አራት አመት ሲሆን በተከታታይ ለሁለት ጊዜ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

18.2 የወረዳ ሸንጎ ሥልጣንና ተግባር

የወረዳው ሸንጎ የወረዳው ከፍተኛ የስልጣን አካል ሲሆን የሚከተሉት ስልጣንና ኃላፊነት አለው፤

1. የፓርቲውን የወረዳ ሊቀመንበር እና የወረዳውን ኡዲትና ምርመራ ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል፣ ይሽራል፣
2. በወረዳው ሊቀመንበር ከወረዳው የፓርቲ አባላት ውስጥ ተመርጠው ለወረዳ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት የቀረቡለትን እጩዎች ብቃት መርምሮ ያፀድቃል፤ ይሽራል፣

3. ከወረዳው ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና ከወረዳው ኦዲትና ምርመራ ኮሚቴ የሚቀርቡለትን የሥራ ክንውን ሪፖርቶች ይመረምራል፣ ያፀድቃል፤ ውሳኔዎችን ይሰጣል፣
4. የወረዳው ሸንጎ ስብሰባ በአመት አንድ ጊዜ ይካሄዳል፣

አንቀጽ 19፡ የወረዳው ኦዲትና ምርመራ ኮሚቴ

1. በወረዳ ደረጃ የፓርቲው ገንዘብና ንብረት በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ዘመናዊ የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ስርአት እንዲዘረጋ ድጋፍ ያደርጋል፣ የወረዳውን የስራ አስፈፃሚ ሪፖርቶች በመመርመር፣ አስተያየትና የማሻሻያ ሀሰቦች ካሉ ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና ለወረዳው ሸንጎ ያቀርባል፣
2. በወረዳው ውስጥ የሚከሰቱ የአባላትም ሆነ የአመራር አካላት የሥነ ሥርዓት ጉዳዮችን የሚያይ የሥነ-ሥርዓት ኮሚቴ ያቋቁማል፣ በሥነ-ሥርዓት ኮሚቴ የተሰጡ ውሳኔዎችን ይግባኝ ይመረምራል የመጨረሻ ውሳኔም ይሰጣል፣ ከወረዳው የፓርቲው አባላት የሚቀርቡ ቅሬታዎችና ጥቆማዎችን መሰረት በማድረግ የአሰራር ጉድለቶች በወቅቱ እንዲታረሙና ችግሮችም እንዲፈቱ የምክርና የሙያ ድጋፍ ያደርጋል፣
3. በፓርቲው የወረዳ መዋቅር ውስጥ በየትኛውም ደረጃ የአሰራር ግድፈት፣ የደንብና መመሪያ ጥሰት አለ ብሎ ሲያምን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይወያያል፣ አስፈላጊው ማስተካካያ እንዲደረግ ለሚመለከተው አካል በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡ ችግሮቹ የማይታረሙ ከሆነ የወረዳው ሸንጎ አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራና በታዩት ችግሮች ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ ያደርጋል፣
4. የወረዳው የኡዲትና ምርመራ ኮሚቴ ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይኖሩታል፣ እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች የስራ ድልድል ያደርጋሉ፣ ከክልሉ የኡዲትና ምርመራ ኮሚቴ ጋር በመተባበር የራሱን የስራ መመሪያ በማዘጋጀት በወረዳው ሸንጎ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣
5. በወረዳው ሸንጎ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፣
6. የወረዳው የኡዲትና ምርመራ ኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን አራት አመት ሲሆን በተከታታይ ለሁለት ጊዜ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

አንቀጽ 20፡ የወረዳ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

20.1: የወረዳ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አመሰራረት እና አሰራር

1. የወረዳ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል
    1. የወረዳ ሊቀመንበር
    2. ምክትል ሊቀመንበር
    3. የኮሚኒኬሽን ጉዳይ ኃላፊ
    4. የአባልነትና አደረጃጀት ጉዳይ ኃላፊ፣
    5. የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ኃላፊ
    6. የሴቶች መማክርት ኃላፊ
    7. የወጣቶች መማክርት ኃላፊ
2. የወረዳው ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ መደበኛ ስብሳባ ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ የሚካሄድ ሲሆን አስቸኳይ ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ሰብሳቢው አስቸኳይ ስብሳባ ሊጠራ ይችላል፣
3. የወረዳ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን አራት አመት ሲሆን በተከታታይ ለሁለት ጊዜ ማገልገል ይችላሉ፡፡

20.2 የወረዳ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር

የወረዳው ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለወረዳው ሸንጎ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፣

1. በወረዳ ደረጃ የፓርቲውን ፕሮግራም፣ ደንብና መመሪያዎች እንዲሁም የክልል እና የወረዳ ሸንጎ ውሳኔዎችን በስራ ላይ ያውላል፣
2. የወረዳውን የስራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ በወረዳው ሸንጎ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣ የስራ እንቅስቃሴውን በተመለከተ ለወረዳው ሸንጎ ሪፖርት ያቀርባል፣
3. ወረዳውን ወክለው ለብሔራዊ፣ ለክልል፣ ለወረዳ እና ለቀበሌ ምክር ቤቶች በምርጫ የሚወዳደሩ የፓርቲውን ዕጩዎች መልምሎ ለወረዳው ሸንጎ ያቀርባል፣ ሲጸድቅ ዝርዝራቸውን ለዞን/ክፍለ-ከተማ አስተባባሪ ይልካል፣
4. በወረዳው ያለውን የህዝብ ፍላጎትና ችግር በማጥናት ለዞን/ክፍለ-ከተማ አስተባባሪ ያሳውቃል፣
5. ከወረዳው ሸንጎ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

አንቀጽ 21፡ የቀበሌ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

21. 1 የቀበሌ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አመሰራረትና አሰራር

1. የቀበሌ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በፓርቲው የወረዳ ሊቀመንበር አቅራቢነት በወረዳው ሸንጎ የሚጸድቁ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

    1. የቀበሌው ሊቀመንበር
    2. ምክትል ሊቀመንበር
    3. የአባልነትና አደረጃጀት ጉዳይ ኃላፊ
    4. የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ኃላፊ
    5. የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ኃላፊ
    6. የሴቶች መማክርት ኃላፊ
    7. የወጣቶች መማክርት ኃላፊ

2. የቀበሌ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ የሚደረግ ሲሆን አስቸኳይ ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ሰብሳቢው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፣
3. የቀበሌ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን አራት አመት ሲሆን በተከታታይ ለሁለት ጊዜ ሊያገለግሉ ይችላሉ፣

21.2፡ የቀበሌ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር

የቀበሌ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለወረዳው ሸንጎ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1. በቀበሌ ውስጥ የፓርቲውን ፕሮግራም፣ ደንብና መመሪያዎች እንዲሁም የፓርቲውን የክልል እና የወረዳ አካላት ውሳኔዎች ስራ ላይ ያውላል፣ ከፓርቲው የበላይ አካላት የሚተላለፉ መመሪያዎችን ለቀበሌው የፓርቲ አባላት በተዋረድ ያስተላልፋል፣
2. የቀበሌውን የስራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ በወረዳው ሸንጎ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ስለ ስራው እንቅስቃሴ ለወረዳው ሸንጎ ሪፖርት ያቀርባል፣
3. ከቀበሌው ነዋሪዎች የሚቀርብለትን የአባልነት ጥያቄ ተቀብሎ ከተሟላ መረጃ ጋር ለወረዳው ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አቅርቦ እንዲጸድቅ ያደርጋል፣ የአባልነት መታወቂያ ካርድ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ በቀበሌው ውስጥ ከሚኖሩ የፓርቲው አባላት የአባልነት ክፍያ ይሰበስባል፣

4. በቀበሌው ያለውን የህዝብ ፍላጎትና ችግር በማጥናት ለወረዳው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና ሸንጎ ያሳውቃል፣
5. ቀበሌውን ወክለው ለቀበሌ ምክር ቤቶች ምርጫ የሚወዳደሩ ዕጩዎችን መልምሎ ለወረዳው ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያስተላልፋል፣
6. ከወረዳው ሸንጎ እና ከውዳው ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

ምዕራፍ ሦስት፡ የብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ተግባርና ኃላፊነት

አንቀጽ 22፡ ሊቀመንበር

የፓርቲው ሊቀ መንበር ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ሆኖ፣

1. የብሄራዊ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ከማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ውስጥ መርጦ ለማዕከላዊ ኮሚቴው በማቅረብ ያስጸድቃል፣ የስራ አስፈጻሚ አባላቱን የስራ አፈጻጸም ይከታተላል፣ በተለያዩ ምክንያቶች ኃላፊነታቸውን መወጣት የማይችሉ አባላት ሲያጋጥም ጉዳዩን ለማእከላዊ ኮሚቴው አቅርቦ ባላቸው የድምጽ ብዛት መሰረት በተጠባባቂ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት እንዲተኩ ያደርጋል፣
2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን ስብሰባዎች ይመራል፣ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ኃላፊነታቸውን በብቃት፣ በታማኝነት፣ በግልጽነት በተጠያቂነት መወጣቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
3. የፓርቲው ፕሮግራም፣ ደንቦች፣ ውሳኔዎችና መመሪያዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣
4. ፓርቲውን በሕጋዊ ሰውነት ይወክላል፣ ውል ይዋዋላል፣ ፓርቲው ከሌሎች አካላት ጋር በሚያደርገው ግንኙነት በፓርቲው የሚጻፉ ደብዳቤዎችና ሰነዶች ላይ ይፈርማል፣ አስተዳደራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የፓርቲው ጽ/ቤት ኃላፊ የደብዳቤ ልውውጦችን እንዲያደርግ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፣
5. የፓርቲውን የስራ እንቅስቃሴ በበላይነት ያስተባብራል፣ ፓርቲውን በመወከል ልዑካን ይመራል፣
6. በስራ አስፈጻሚው ውሳኔ መሰረት የፓርቲው የባንክ ሂሳብ እንዲከፈት ለሚመለከታቸው ባንኮች ደብዳቤ በመጻፍ የባንክ ሂሳብ እንዲከፈት ያደርጋል፣ የባንክ ሂሳቦቹን ከፓርቲው ከፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ኃላፊ ወይም ከፓርቲው ጽ/ቤት ኃላፊ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፣
7. በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስር የሚቋቋሙ ቋሚና ጊዚያዊ ኮሚቴዎችን የዕለት ከዕለት ተግባራት ይከታተላል፣
8. ሊቀመንበሩ በብሄራዊ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስምምነት ልዩ የዘርፍ አማካሪዎች ይኖሩታል፡፡
9. **የፓርቲው ሊቀመንበር አመራረጥ**
    1. ለሊቀመንበርነት መወዳደር የሚፈልጉ የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ራሳቸውን በእጩነት ያቀርባሉ ወይም የጠቅላላ ጉባኤ አባላት እጩ በጥቆማ ያቀርባሉ፣
    2. ዕጩ ሊቀመንበር የሚጠቁሙ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት የጠቆሙትን ሰው በተመለከተ አጭር መረጃ ለጉባኤው ይሰጣሉ፤

አንቀጽ 23፡ ምክትል ሊቀመንበርና የምርጫ ጉዳይ ኃላፊ

የፓርቲው ምክትል ሊቀመንበር ከስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት መካከል በፓርቲው ሊቀመንበር አቅራቢነት በፓርቲው ማእከላዊ ኮሚቴ የሚጸድቅ ሲሆን ተጠሪነቱ ለፓርቲው ሊቀመንበር ይሆናል፡፡ ምክትል ሊቀመንበሩ የሚከተሉት የስራ ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

23.1 በምክትል ሊቀመንበርነት

1. በፓርተው አጠቃላይ እንቅስቃሴ ላይ ሊቀመንበሩን ይረዳል፣ ያማክራል፣ ሊቀመንበሩ በሌሉበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፣

2. ከሊቀመንበሩ ጋር በመነጋገር በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚቋቋሙ ቋሚና ጊዚያዊ ኮሚቴዎችን የስራ እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣
3. ከሊቀመንበሩ ጋር በመስማማት ከክልል ማስተባባሪያ ጽ/ቤቶች ውስጥ የተወሰኑት ክልሎችን የስራ እንቅስቃሴ ይከታተላል ያስተባብራል፣
4. ከሊቀመንበሩ ጋር በመስማማት ከስራ አስፈጻሚ የስራ ኃላፊነቶች ውስጥ የተወሰኑ የስራ ክፍሎችን ያስተባብራል፣
5. በሊቀመንበሩና በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ስራዎች ይሰራል።

23.2 በምርጫ ጉደይ ኃላፊነት

1. በሀገር አቀፍ፣ በክልል፣ በወረዳና በቀበሌ ም/ቤቶች ፓርቲውን ወክለው ለምርጫ የሚቀርቡ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን መመዘኛና የሥራ መመሪያ ያዘጋጃል፣ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ለምርጫ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መመዝገባቸውን ያረጋግጣል፣
2. የምርጫው ጊዜ ከመድረሱ በፊት የፓርቲውን የምርጫ ማኒፌስቶ ለፓርቲው አባላት፣ ደጋፊዎችና ለህዝብ እንዲሰራጭ ያደርጋል፣ በየደረጃው የሚገኙ አባላትም በምርጫው ዙሪያ በቂ ስልጠናና ትምህርት ማግኘታቸውን ያረጋግጣል፣
3. የፓርቲውን የምርጫ ታዛቢዎች መመዘኛ፣ ተግባርና ኃላፊነት፣ አመዳደብ፣ የስነ-ምግባር መመሪያ ወዘተ ያዘጋጃል፣
4. ከምርጫና ከተመራጮች እንቅስቃሴ ጋር በተያየዘ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት ከሚመለከታቸው የመንግስትና ሌሎች አካላት ጋር ይነጋገራል፣
5. ከምርጫ ጋር በተያያዘ መረጃ ያጠናቅራል፣ የውጭ
6. ከሊቀመንበሩ እና ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

አንቀጽ 24፡ የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ኃላፊ

የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ኃላፊ ተጠሪነቱ ለፓርቲው ሊቀመንበር ሆኖ፤

1. የፓርቲውን የፐሬስ መግለጫዎችና የፐሬስ ኮንፈረንሶችን ያዘጋጃል፣ የፓርቲው ቃል አቀባይ በመሆን ያገለግላል፣ ፓርቲው የሚያከናውናቸውን ልዩ ልዩ ተግባሮች ለሕዝብ ያሳውቃል፣ ከሊቀመንበሩ ጋር በመመካከር እንደ አስፈላጊነቱ በልዩ ልዩ የኃላፊነት ደረጃ ላይ ያሉ የፓርቲው አመራራ አካላት መግለጫ እንዲሰጡ ያደርጋል፣
2. ቅስቀሳን የሚመለከቱ ስራዎችን ያቅዳል በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሲጸድቅ ይፈጽማል፣ አውደ ጥናቶችና ህዝባዊ ስብሰባዎችን እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ያስተባብራል፣ የፓርቲውን የኢዲቶሪያል ፓሊሲና የስራ መመሪያ አዘጋጅቶ በስራ አስፈጻሚ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣
3. የፓርቲውን ልሳን የሚመራ ኢዲቶሪያል ክፍል እንዲቋቋም ያደርጋል፣ የፓርቲውን ልሳን፣ የሶሻልሚዲያ እና ሌሎች የኮሚኒኬሽን ፕላትፎርሞች ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣
4. የቅስቀሳ ጽሁፎች፣ በራሪ ወረቀቶች ወዘተ እንዲዘጋጁና እንዲሰራጩ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች ተገቢ በሆኑ ቦታዎች እንዲተከሉ ያደርጋል፣ የቅስቀሳና ማስታወቂያ ስራውን ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ የስነ ጥበብና/ኪነ-ጥበብ ስራዎች ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣
5. ከሊቀመንበሩ እና ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ 25፡ የአባልነትና ድርጅት ጉዳዮች ኃላፊ

የአባልነትና ድርጅት ጉዳዮች ኃላፊ ተጠሪነቱ ለፓርቲው ሊቀመንበር ሆኖ፣

1. በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች የፓርቲው መዋቅር የሚዘረጋበትንና ፅህፈት ቤቶች የሚከፈቱበትን ጥናት ያካሂዳል፣ የጽህፈት ቤቶች የስራ መመሪያ ያዘጋጃል፣

2. የፓርቲውን ስራ በሚያግዝ መልኩ የተለያዩ የአደረጃጀት እና ተያያዥ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ የፓርቲው አደረጃጀት በሰው ኃይል፣ በቴክኖሎጂ፣ በመዋቅርና በአሰራር ጠንካራ እንዲሆን ስርዓት ይዘረጋል፣ በስራ አስፈጻሚ ሲጸድቅ ይተገበራል፣
3. የአባልነት ምልመላ፣ ምዝገባና አስተዳደር ዘመናዊ እና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ ማካሄድ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፣ የአባላት መብት እና ግዴታ መከበሩን ይቆጣጠራል፣ የፓርቲው አባላት ቁጥርና አቅም በየግዜው የሚያድግበትን መንገድ ይቀይሳል፣ የአባላት ማሕደሮች በአግባቡ እንዲደራጁና እንዲጠበቁ ያደርጋል፣
4. ከሲቪል እና ከግሉ ዘርፍ እንዲሁም ከሌሎች የማህበረሰብ አካላት ጋር በጋራ የሚሰራበትን አደረጃጀት ይቀይሳል፣
5. የፓርቲውን አባላት እና ደጋፊዎች አቅም ለመገንባት እና የፖለቲካ ግንዛቤን ለማዳበር ስልጠናዎችን ያዘጋጃል፣
6. በአባላት መካከል የመቀራረብና የአንድነት መንፈስን የሚያጠናክሩ ግንኙነቶች እንዲፈጠሩ፣ የአባላት ማህበራዊ ግንኙነትና መስተጋብር እንዲጠነክር ስልቶች ይዘረጋል፣
7. የድርጅቱንና የአባላትን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ የአሰራር ስርአቶችን ይዘረጋል፣
8. ከሊቀመንበሩ እና ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

አንቀጽ 26፡ የውጪ ጉዳይ እና ዲያስፖራ ኃላፊ

የውጪ ጉዳይ እና ዲያስፖራ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለፓርቲው ሊቀመንበር ሆኖ፣

1. ከኢትዮጵያ ውጪ የሚገኙ አባላትና ደጋፊዎችን ጉዳይ ይከታተላል፣ በሚገኙባቸው አካባቢዎች እንዲደራጁ ያደርጋል፣ እንቅስቃሴያቸውንም ይከታተላል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣
2. በውጭ ሀገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ያሉባቸውን ችግሮች ይከታተላል፣ ችግሮቻቸው የሚፈቱበትን መንገዶች ይቀይሳል፣ ለጉዳዩ ቅርበት ካላቸው አካላት ጋር ይወያያል፣
3. በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚኖሩ የዲፕሎማቲክ አባላት ፓርቲውን ለማስተዋወቅ እና በጋራ አጀንዳዎች ላይ ለመስራት የሚያስችሉ አሰራሮችን ይቀይሳል፣ በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተቀባይነት ሲያገኝ ይፈጽማል፣
4. ከተለያዩ መንግስታት፣ አለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የፓርቲውን ዓላማ ያስተዋውቃል፣ ድጋፍ ያሰባስባል፣
5. ከሌሎች አገሮች አቻ የፓለቲካ ፓርቲዎች ጋር የወዳጅነት ግንኙነት እንዲመሰረትና የልምድ ልውውጥ መድረኮች እንዲዘጋጁ ጥረት ያደርጋል፣
6. የኢትዮጵያን የውጭ ጉዳይ መርሆችን ያጠናል፣ በውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ዙሪያ ለፖሊሲ አቅጣጫ የሚሆኑ ጹሁፎችን ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል ፣
7. ከሊቀመንበሩ እና ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፣

አንቀጽ 27፡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ኃላፊ

ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ኃላፊ ተጠሪነቱ ለፓርቲው ሊቀመንበር ሆኖ፣

1. በሀገሪቱ ውስጥ የሚከናወኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁነቶችን በመከታተል ወቅታዊ ሪፖርቶችን ያዘጋጃል፣ ለሚመለከታቸው የፓርቲው አካላት እንዲደርስ ያደርጋል፣
2. በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ዙሪያ የፓርቲውን የፖሊሲ አቅጣጫዎች ያጠናል፤ የፖሊሊ አቅጣጫዎች ያቀርባል፣
3. በተለያየ ግዜ እና ቦታ በሚካሄዱ ባህላዊና ማህበራዊ ፕሮግራሞች ፓርቲውን ወክሎ ይሳተፋል፣
4. ከተለያዩ ማህበራዊ ተቋማት ጋር ለጋራ ዓላማ በትብብር የሚሰራበትን ሁኔታዎችና መድረኮች ያመቻቻል፣
5. ወሳኝ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምር እንዲካሄድ ያበረታታል፣ የጥናት ውጤቶች ለፓርቲው አመራርና አባላት እንዲሁም ለህዝብ የሚደርስበትን ሁኔታ ይቀይሳል፣

6. ትምህርት፣ ጤና፣ ትራንስፖርት፣ ውሀ፣ መብራት የመሳሰሉ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ሽፋን፣ ጥራት አቅርቦትን በተመለከተ መረጃ ያጠናቅራል፣ ያሰራጫል፣ አገልግሎቶቹ ዝቅተኛ በሆኑባቸው አካባቢዎች አገልግሎቶቹን ከፍ ለማድረግ ከመንግስት፣ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የልማት ፕሮጀክቶች እንዲታቀዱ እና እንዲተገበሩ ይሰራል፣
7. ምርት፣ አጠቃላይ ዋጋ፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ንግድ፣ የመንግስት በጀትና ብድር የመሳሰሉ ምጣኔ ሀብታዊ ጠቋሚዎችንና መለኪያዎችን በተመለከተ መረጃ ያሰባስባል፣ ይተነትናል ያሰራጫል፣
8. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሀይማኖታዊ ተቋማትና በዓላት ላይ በመገኘት የእምነት እና የአምልኮ ነጻነቶች እንዲከበሩ ምክረ ሀሳብ ይሰጣል፣ በተለያዩ እምነት ተከታዮች መካከል መግባባትና መቻቻል እንዲፈጠር ድጋፍ ያደርጋል፣ ከሀይማኖት ምሁራን ጋር ፓርቲውን ወክሎ ውይይት ያደርጋል፣
9. ማህበራዊ መስተጋብርን ለማነልበትና በህዝቦች መካከል ባህላዊ ትስስርን ለማጠናከር የሚያግዙ ሀሳቦችን ያመነጫል፣ ተግባራዊ እንዲሆኑ ይሰራል፣

አንቀጽ 28፡ የጥናትና ስትራቴጂ ጉዳይ ኃላፊ

የጥናትና ስትራቴጂ ጉዳይ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለፓርቲው ሊቀመንበር ሆኖ፣

1. ለፓርቲው ስራ የሚሆኑ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ የመረጃ ማዕከል ያቋቁማል፣ በፓርቲው ርዕዩተ ዓለም፣ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ላይ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣ ሰነዶች ያዘጋጃል፣
2. የፓርቲውን የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅድ፣ ስልትና ስትራቴጂ ያዘጋጃል፣
3. በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የፓርቲው አመራር አባላት በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በስትራቴጂ እና በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያስችል የተለያዩ የስልጠናና የአቅም ግንባታ ስልቶችን ይቀይሳል፣
4. ፓርቲው የፖሊሲ ጉዳዮችን በጥልቀት የሚያጠና በባለሙያዎች የተደራጀ የፖሊሲ ጥናት ተቋም ይኖረዋል፡፡ የተቋሙን አደረጃጀትና አስተዳደር በጥናትና ስትራቴጂ ጉዳይ ተጠንቶ በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሲጸድቅ ተግባራዊ ይሆናል፣
5. ፓርቲው የትግል አድማሱን ማስፋፋት የሚችልበትን ስልትና ስትራቴጂ ይቀይሳል፣ በፓርቲው እንቅስቃሴና የትግል ውጤት ላይ ተፅዕኖ ሊያደርጉ የሚችሉ ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎችን በመለየት፣ በመተንተንና፣ በከብደታቸው ቅደም ተከተል በማስቀመጥ የተለያዩ ስልቶችና አቅጣጫዎችን ይቀይሳል፣
6. የተለያዩ አለማቀፋዊ፣ አካባቢያዊና አገራዊ ሁኔታዎችን የኃይል አሰላለፎችን በመገምገም በፓርቲው እንቅስቃሴና የትግል ውጤት ላይ ሊኖራቸው የሚችለውን እንድምታ ይተነትናል፣
7. በሊቀመንበሩ እና በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

አንቀጽ 29፡ የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ኃላፊ

የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ኃላፊ ተጠሪነቱ ለፓርቲው ሊቀመንበር ሆኖ፣

1. ለፓርቲው የገቢ ምንጭ ያጠናል፣ የገቢ ማስገኛ ዝግጅቶችን ያስተባብራል፣ በበላይነት ይመራል፣
2. የፓርቲውን የገቢና የወጪ ዝርዝር የያዘ ዓመታዊ የፋይናንስ ዕቅድ በየበጀት ዓመቱ ያዘጋጃል፣ በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ የፓርቲውን ገቢና ወጪ ዝርዝር የሚያሳይ የሂሳብ መግለጫ በማዘጋጀት ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እና ለኦዲትና ምርምር ኮሚሽን ያቀርባል፣

3. የፓርቲው ገንዘብና ንብረት በትክክል እንዲጠበቅና በአግባቡ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ የሂሳብ አያያዝና የንብረት አጠባበቅ ስልቶችን ይቀይሳል፣ የፓርቲው ሂሳብ አያያዝ በሕግ ተቀባይነት ያለው የሂሳብ አሰራር የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል፣
4. በየደረጃ ያሉ የፓርቲው ጽ/ቤቶች የሚሰበሰቡትን ማንኛውንም ገንዘብ አጠቃቀምና አስተዳደር፣ የፓርቲው አጠቃላይ የገንዘብና የንብረት አጠቃቀም ሥርዓት ያዘጋጃል፣
5. ሁሉም የፓርቲው መዋቅሮች የሚተዳደሩበት የፓርቲውን የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ደንብ፣ የገንዘብና የንብረት አያያዝ መመሪያ ያዘጋጃል/እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ በሥራ አስፈፃሚው ሲፀድቅ በስራ ላይ ያውላል፣
6. በሊቀመንበሩ እና በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ 30፡ የሕግ ጉዳዮች ኃላፊ

የሕግ ጉዳዮች ኃላፊ ተጠሪነቱ ለፓርቲው ሊቀመንበር ሆኖ፣

1. ፓርቲውን በመወከል ወይንም ጠበቃ በመቅጠር በማንኛውም ፍ/ቤት ወይም መንግስታዊ አካል ፊት ክስ ይመሰርታል፣ ይከላከላል፣ ይከራከራል፣ ይግባኝ ያቀርባል፣ እንዲሁም የፍርድ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣
2. የፓርቲው አባላት መብቶች በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት መከበራቸውን ያረጋግጣል፣ የአሰራር ግድፈት ሲኖር እንዲስተካከሉ ያደርጋል፣
3. አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፣ ለተለያዩ የፓርቲ አካላትና አባላት ከፓርቲው ስራ ጋር በተያያዘ የሕግ ምክርና ድጋፍ ይሰጣል፣
4. ፓርቲውን በሚመለከት በማንኛውም የሕግ ጉዳይ ላይ ኃላፊ ሆኖ ይሰራል፣ በፓርቲው ሰነዶችም ላይ የሕግ አስተያየት ይሰጣል፣
5. ከፓርቲው የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን እንዲሁም በተዋረድ ካሉ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚዎች ጋር ህግ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በጋራ ይሰራል፤
6. በሊቀመንበሩ እና ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ 31፡ የሴቶች መማክርት ኃላፊ

ሴት የፓርቲው ዓባላት በፍላጎታቸው የፓርቲው የሴቶች መማክርት አባል መሆን ይችላሉ። የሴቶች መማክርት አባል ለመሆን የመማክርቱን የአባልነት ፎርም ሞልቶ መመዝገብ ያስፈልጋል። የመማክርቱ ኃላፊ ተጠሪነቷ ለፓርቲው ሊቀመንበር ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ኃላፊነት አሏት፣

1. ሴቶች በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ፣ በባህላዊና በጥበብ መስኮች የላቀ ተሳትፎ እንዲኖራቸው፤ የሚያስችል የስርአተ- ፆታ ጥናቶችን ማጥናት ወይም እንዲጠና ማድረግ፣ የፖሊሲ ረቂቅ ማዘጋጀት፣
2. የፓርቲው አጠቃላይ እንቅስቀሴ ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘበ መሆኑን መከታተል፣ የፓርቲው አባላት ስለ ሥርዓተ- ፆታ ያላቸው ግንዛቤ የሚዳብርበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
3. ሴቶች መብቶቻቸውን ለማስከበር በማህበር እንዲደራጁ ማበረታታት፣ በሴቶች ዙሪያ ከሚሰሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችሉ መድረኮችን ማዘጋጀት፣
4. በሀገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ ሴቶችን አስመልክቶ የሚዘጋጁ መድረኮች ላይ ፓርተውን በመወከል መሳተፍ፣
5. በሀገር ደረጃ የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ደንቦችና መመሪዎች የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ያገናዘቡ እንዲሆኑ ጉትጎታ (Advocacy) ማድረግ፣ ማማከር፣
6. ሴቶችን በተመለከተ ያሉ የተሳሳቱ አመለካከቶችና ጎጂ ባህሎች እንዲወገዱ ከባለድርሻ አካላት ጋር መስራት፣
7. በሊቀመንበሩ እና ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ 32፡ የወጣቶች መማክርት ኃላፊ

የወጣቶች መማክርት አስፈላጊነት

የወጣቶች መማክርት ዓላማ ወጣት የፓርቲው አባላት የአመራር አቅማቸውን እንዲያዳብሩ፣ የአደረጃጀት እና የአስተዳደር ልምድ እንዲያካብቱ፣ በእውቀት፣ በስነልቦና፣ በስነምግባርና በአመለካከት እንዲጎለብቱ በማድረግ የፓርቲውን ተተኪ አመራር ለመፍጠር እገዛ ማድረግ ነው፡፡ የወጣቶች መማክርት አባላት ወጣቱን በሚመለከቱ ሀገራዊና ዓለም ዓቀፋዊ ጉዳዮች ላይ በነጻነት እንዲወያዩ እና እርስ በርስ እንዲማማሩ እድል ይሰጣል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

የወጣቶች መማክርት አባላትና አመሰራረት

1. ከፓርቲው አባላት ውስጥ እድሜው ከ 30 አመት ያልበለጠ የፓርቲው የወጣቶች መማክርት አባል መሆን ይችላል፣ እድሜው ከ30 ዓመት በላይ የሆነ የፓርቲው አባል ከወጣቶች መማክርት አባልነት ይወጣል፣
2. የወጣቶች መማክርት አባልነት በፍላጎት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ማንኛውም የወጣቶች መማክርት አባል የፓርቲው አባላት ያላቸው መብትና ግዴታ አለው/አላት፣

የወጣቶች መማክርት ስልጣንና ኃላፊነት

የፓርቲው የወጣቶች መማክርት ተጠሪነቱ ለፓርቲው ሊቀመንበር ሆኖ፣

1. ወጣቶች በፓርቲው ውስጥ የነቃና ሙሉ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችል አሰራርና ስርዓት ይዘረጋል፣
2. ወጣቱ ከነጂ ባህሎችና ልማዶች እንዲርቅና አገራዊ ራዕይና መልካም ሥነ- ምግባር እንዲኖረው የሚረዱ ስልቶችን ይቀይሳል፣
3. የመማክርቱ አባላትም ሆኑ አባል ያልሆኑ ወጣቶች በስፖርትና በስነ ምግባር እንዲታነጹ፣ በስነ-ጾታና በጾታ ዲሲፕሊን በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን ይነድፋል፣ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ ያደርጋል፣
4. ወጣቶች ለትምህርት፣ ለምርምር እና ለፈጠራ ፍቅር እንዲኖራቸው ድጋፍ ያደርጋል፣ ወጣቶች እንዲደራጁ ያግዛል፣ ፓርቲው ከወጣት ማህበራት ጋር የጠነከረ ግንኙት እንዲኖረው ይጥራል፣
5. በሊቀመንበሩ እና ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

ምዕራፍ አራት፡ የፓርቲው ልዩ ልዩ አካላት

አንቀጽ 33፡ የፓርቲው ጽሕፈት ቤት ኃላፊ

የፓርቲው ጽሕፈት ቤት ኃላፊ በሙያ ብቃት ተመርጦ የሚቀጠር ቋሚ የፓርቲው ሰራተኛ ሲሆን፣ ተጠሪነቱ ለሊቀመንበሩ ይሆናል፡፡ የጽ/ቤቱ ኃላፊ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፣

1. የፓርቲውን ፅሕፈት ቤት ያደራጃል፣ የእለት ከእለት ሥራውን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣
2. ለፓርቲው ዋና መስሪያ ቤት መዋቅር፣ የቋሚ እና ግዚያዊ ሰራተኞች ቅጥርና አስተዳደር መመሪያ ያዘጋጃል፣ ከሊቀመንበሩ ጋር በመመካከር የባለሙያና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ፍላጎት ያጠናል፣ በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሲጸድቅ ሰራተኞችን ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፣
3. ከሊቀመንበሩ ጋር በመመካከር የጽህፈት ቤቱን የደብዳቤ ልውውጦችን ያከናውናል፣ የጽህፈት ቤቱ ሰነዶችና ማህተም በስርዓት መያዛቸውንና መጠበቃቸውን ያረጋግጣል፣
4. የፓርቲው ጽ/ቤት ለስራ ምቹ ይሆን ዘንድ አስፈላጊውን ቁሳቁስ፣ ቴክኖሎጂና ሌሎች ቋሚና አላቂ እቃዎች እንዲሟሉ ያደርጋል፣
5. ስለ ፕሮቶኮል ጉዳዮች ዝርዝር የአፈፃጸም ስልቶችን በማዘጋጀት በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሲፀድቅ ይፈጽማል፣

6. ስለ ጽሕፈት ቤቱ የስራ እንቅስቃሴ ለሊቀመንበሩ ሪፖርት ያቀርባል፣
7. በሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ 34፡ የሕዝብ ተመራጮች

1. በሐገር አቀፍ፣ በክልል፣ በዞን/ከፍለ ከተማ፣ በወረዳ/ከተማና ቀበሌ ምክር ቤቶች ፓርቲውን ወክለው የሚሳተፉ የሕዝብ ተመራጮች በየደረጃው ባሉበት ምክር ቤት ስብስብ ይፈጥራሉ፣ የየራሳቸውን የምክር ቤት ተጠሪዎች ይሰይማሉ፣
2. ከፓርቲው እና ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር የሚኖራቸው የስራ ግንኙነትና አሰራር የማዕከላዊ ኮሚቴው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

አንቀጽ 35፡ የአማካሪዎች ሸንጎ

1. በማዕከላዊ ኮሚቴ የሚመረጡ ከዘጠኝ የማይበልጡ አባላት ያሉት በዕውቀታቸው፣ በስራ ልምዳቸው፣ በዕድሜቸውና ከህብተሰቡ ጋር ባላቸው ቅርብ ትስስር፣ በመልካም ተግባራቸው ታዋቂ የሆኑ ግለሰቦችና የአገር ሽማግሌዎች፣ የኃይማኖት፣ የባህላዊና ተመሳሳይ ተቋማት መሪዎችን የሚያካትት የአማካሪዎች ሸንጎ ይቋቋማል፣
2. የአማካሪ ሸንጎው ፓርቲው በሚያደርጋቸው የስራ እንቅስቃሴዎች ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን የሚረዱ ምክሮችና ልምዶችን ለፓርቲው አመራርና አባላት ያካፍላሉ፣ ፓርቲው በሀገር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነቱና ተአማኒነቱ ከፍ እንዲል ድጋፍ ያደርጋሉ፣
3. የሸንጎው አባላት ፓርቲው በሚያዘጋጃቸው ሙያዊና ህዝባዊ መድረኮች በመገኘት የህይወት ተሞክሯቸውንና ልምዳቸውን ያካፍላሉ፣
4. ለፓርቲው ልዩ ልዩ አካላት፣ በሀገር አቀፍ በክልል እና በወረዳ ለሚገኙ የፓርቲው አመራርና አባላት ሙያ እና ልምዳቸውን ያካፍላሉ፣
5. አማካሪ ሸንጎው ስብሰባ ሲያደርግ በቅድሚያ ከሸንጎው አባላት ሰብሳቢ ይመርጣል። የፓርቲው ጽ/ቤት ኃላፊ የሸንጎው ጸኃፊ ሆኖ ይሰራል።

ምዕራፍ አምስት፡ ጥፋቶችና ውሳኔ አሰጣጥ

አንቀጽ 36፡ የጥፋት አይነቶች

ቀላል የሥነ ሥርዓት ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች

1. የፓርቲውን የአሰራር ደንቦችና መመሪያዎች አለማክበርና መጣስ፣
2. በፓርቲው አባልነትና በሕዝብ የተሰጠውን ኃላፊነትና ግዴታ አለመወጣት፣
3. የአባልነት መዋጮና ሌሎች ከአባላት የሚጠበቁ ድጋፍና አስተዋጾ ሆን ብሎና በተደጋጋሚ አለመፈጸም፣
4. የፓርቲውን ሥራ ሆን ብሎ ለማጓተት የተሰጠውን ተግባር በአግባቡ አለመስራት፣
5. የባህል፣ ቋንቋ፣ እምነት ወዘተ ልዩነቶችን በተደጋጋሚ ባለማክበር የፓርቲውን አባላት ስሜትና የስራ ሞራል የሚነዳ ንግግርና ተግባር የሚፈጽም።

ከባድ የሥነ ሥርዓት ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች

1. የፓርቲውን ስልጣንና ኃላፊነት በመጠቀም ወይም በአገር ደረጃ የተሰጠውን የሕዝብ ሥልጣን በመጠቀም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አግባብ ያልሆነ ጥቅም ያገኘ ወይም ለሌሎች የማይገባ ጥቅም የሰጠ ወይም ሌሎችን የሚጎዳ ተግባር የፈፀመ፣
2. ብሄርን፣ ዘርን፣ ኃይማኖትን፣ ዝምድናን ወዘተ መሠረት በማድረግ በፓርቲው ውስጥ ሹመት ወይም ምደባ ያደረገ፣ በሥራ ላይ አድልዎ የፈፀመ፣

3. የድርጅቱን ገንዘብ እና ሀብት ለግል ጥቅሙ ያዋለ፣ ያባከነ ወይም ያጠፋ፣ የፓርቲውን ሰነድና ማህተም በመጠቀም ሕገ-ወጥ ድርጊት የፈፀመ፣ የፓርቲውን ስብሰባዎች ቃለ-ጉባኤና ዶክመንቶች ያለፈቃድ ወይም የሚመለከተው አካል ይፋ ሳያደርጋቸው አስቀድሞ በፅሑፍ ወይም በማንኛውም ዘዴ ለሌላ ወገን ያስተላለፈ፣
4. የሌላ የፖለቲካ ፓርቲ አባል ሆኖ የተገኘ ወይም በሌላ ፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ ተቀጥሮ የሰራ፣
5. በሕፃናት እና በሴቶች ላይ ወሲባዊ ጥቃት ወይም ትንኮሳ የፈፀመ፣
6. ከላይ ከተመለከቱት ከባድ የሥነ ሥርዓት ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች ጋር ተቀራራቢ የሆኑ ጥፋቶችን የፈጸመ።

አንቀፅ 37፡ የክስ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት

1. ማንኛውም የፓርቲው አባል እንዲሁም የፓርቲው ተቋም በማንኛውም የፓርቲው አባል ወይም ተቋም ላይ አግባብነት ላለው የሥነ-ሥርዓት ኮሚቴ ክስ የማቅረብ መብት አለው፣
2. የሥነ-ሥርአት ክስ የሚያቀርቡ ሁሉ ክሱን ወይም ምላሹን ራሳቸው ማቅረብና መከታተል ወይም ጠበቃ መወከል ይችላሉ፣

አንቀፅ 38፡ የሥነ-ሥርዓት ኮሚቴዎች አወቃቀር

1. የሥነ-ሥርዓት ክሶችን ለመስማት የሥነ-ሥርዓት ኮሚቴዎች በብሔራዊ የኡዲትና ምርመራ ኮሚሽን እንዲሁም በክልል፣ በወረዳ እና ቀበሌ ደረጃ ባሉ የኡዲትና ምርመራ ኮሚቴ አማካኝነት ይቋቋማሉ፣
2. ሥነ-ሥርዓት ኮሚቴ አባላት ቁጥር በብሔራዊ እና ክልል ደረጃ 5፣ በወረዳና ቀበሌ 3 ይሆናሉ፣
3. የሥነ-ሥርዓት ክሶችን ለመስማት ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ እንደተሟላ ይቆጠራል፣ ውሳኔ በድምፅ ብልጫ ይወሰናል፣
4. የሥነ-ሥርዓት ኮሚቴዎች ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀኃፊ ይኖራቸዋል፣ ፀኃፊው የኮሚቴውን ክስ ስሚና ይግባኝ ቃለ ጉባዔ ይይዛል፣
5. የሥነ-ሥርዓት ኮሚቴ የሥራ ዘመን 4 ዓመት ሲሆን ለሁለት ተከታታይ የስራ ዘመን ማገልገል ይችላሉ።

አንቀፅ 39፡ የክስ አቀራረብ እና ክስ መስማት ሥነ- ሥርዓት

1. አንድ የፓርቲው አባል ወይም ተቋም የስነ-ስርዓት ክስ ሲቀርብበት ክሱ እና ማስረጃዎቹ ከመጥሪያ ጋር ከ 5 (አምስት) ቀን ቀደም ብሎ ሊደርሰው ይገባል፣
2. የሥነ- ሥርዓት ክስ በሚሰማበት ቀን ክሱ ይነበብለታል፣ ጥፋተኛ እንደሆነ እና እንዳልሆነ ይጠየቃል። ጥፋተኛ ነኝ ካለ ወዲያውኑ ውሣኔ ይሠጣል፣ ጥፋተኛ አይደለሁም ካለ ምላሹን በጽሑፍ ወይም በቃል እንዲሰጥና ማስረጃዎችን የመስማት ወይም የማየት ሂደት ይቀጥላል።
3. የስነ-ሥርዓት ክስ የቀረበበት ሰው መጥሪያው ደርሶት ክስ በሚሰማበት ቀን ያልተገኘ እንደሆነ በኮሚቴው ውሳኔ መሰረት ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ሊደረግ ይችላል፣
4. ማንኛውም የሥነ-ሥርዓት ክስ የቀረበበት አባል ወይም ተቋም ውሣኔ አስከሚሰጥበት ቀን ድረስ እንደ ጥፋተኛ አይቆጠርም፣

አንቀፅ 40፡ ውሣኔ አሰጣጥ እና የይርጋ ጊዜ

1. ምስክሮች ከተሰሙ እና ማስረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ የሥነ-ሥርአት ኮሚቴው የግራ ቀኙን መከራከሪያ በአግባቡ ከመረመረ በኋላ ውሳኔ ይሰጣል፣ ኮሚቴው ውሣኔ እንደወሰነ ቢበዛ በ 5 (አምስት) ቀናት ውስጥ ውሣኔውን ለሚመለከተው የኡዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ/ኮሚሽን ያሳውቃል፣
2. ማንኛውም የሥነ-ሥርዓት ክስ ጥፋቱ መፈፀሙ ከታወቀበት ጊዜ አንስቶ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት። በሶስት ወር ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል።

አንቀፅ 41፡ ቅጣት

የሥነ-ሥርአት ኮሚቴው ጉዳዩን ተመልክቶ ተከሳሽ በቀረበበት ክስ መሠረት ጥፋት ፈጽሟል ብሎ ሲወስን የጥፋቱን ክብደትና ቀላልነት በማገናዘብ፤

1. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ቀላል የሥነ ሥርዓት ጥፋቶች ተብለው የተዘረዘሩትንና ተቀራራቢ ቀላል ጥፋቶችን የፈፀመ ከተግሳጽ ጀምሮ የቃል ወይም የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ወይም የገንዘብ መቀጮ መወሰን ይቻላል፡፡
2. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ከባድ የሥነ ሥርዓት ጥፋቶች ተብለው የተዘረዘሩትንና ተቀራራቢ ከባድ ጥፋቶችን የፈጸመ አባል ከአባልነት ሊታገድ፣ ከኃላፊት ሊነሳ፣ ወይም ከፓርቲው አባልነት ሊሰረዝ ይችላል፣ የሥነ-ሥርአት ጥፋቱን የፈጸመው የጠቅላላ ጉባኤ አባል ከሆነ ውሳኔው በጠቅላላ ጉባኤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ይሆናል፣
3. የሥነ-ሥርአት ኮሚቴው ጥፋት በፈጸመው አካል የተበደለ ሰው ካለ ተከሳሹ ተበዳዩን በገንዘብ እንዲከስ ሊወስንበት ይችላል፡፡

አንቀፅ 42፡ ይግባኝ

የአዲትና ምርመራ ኮሚሽን/ኮሚቴዎች ይግባኝ ሰምተው የመጨረሻ ውሣኔ የሚሰጡ ሲሆን የሥነ-ሥርአት ውሳኔው ተግባራዊ የሚሆነው የይግባኝ ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ነው፡፡ ማንኛውም ውሣኔ የተወሰነበት ወገን ውሳኔው በይግባኝ እንዲታይለት የሚፈልግ ከሆነ በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ይግባኝ ማቅረብ አለበት፡፡

1. የወረዳ አዲትና ምርመራ ኮሚቴ በቀበሌ እና በወረዳ የሥነ-ሥርዓት ኮሚቴዎች የተወሰነን የሥነ-ሥርዓት ውሳኔ ተመልክቶ ውሳኔ ይሰጣል፣
2. የክልል አዲትና ምርመራ ኮሚቴ በክልል የሥነ-ሥርአት ኮሚቴ እና በወረዳ የአዲትና ምርመራ ኮሚቴ የተወሰነን የሥነ-ሥርዓት ውሳኔ ተመልክቶ ውሳኔ ይሰጣል፣
3. የብሔራዊ አዲትና ምርመራ ኮሚሽን በብሄራዊ የሥነ-ሥርአት ኮሚቴ እና በክልል የአዲትና ምርመራ ኮሚቴ የተወሰነን የሥነ-ሥርዓት ውሳኔ ተመልክቶ ውሳኔ ይሰጣል፣
4. አንድ ክስ በሁለት ተከታታይ ውሳኔ ሰጭ እርከኖች ላይ ተመሳሳይ ውሳኔ ካገኘ ይግባኝ አይጠየቅበትም፡፡ ሆኖም ውሳኔው ከተሻሻለ ወይም ከተለወጠ ለሚቀጥለው አካል ይግባኝ ማለት ይቻላል፣ በይግባኝ አዲስ ክስ ሊቀርብ አይችልም፣
5. ይግባኝ ሰሚው አካል የበታች ኮሚቴውን ውሳኔ ሊያፀድቀው፣ ሊያሻሽለው ወይም ሊለውጠው ይችላል፣
6. በፓርቲው የሥነ-ሥርዓት ኮሚቴና በፓርቲው የይግባኝ ሰሚዎች ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል በመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ የመመስረት መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ምዕራፍ ስድስት፡ የፓርቲው የገቢ ምንጭ

አንቀጽ 43፡ የፓርቲው የገቢ ምንጮች

የፓርቲው የገቢ ምንጮች የሚከተሉት ናቸው፤

- የአባልነት መዋጮ፣
- ከኢትዮጵያውያን ግለሰቦችና ኩባንያዎች የሚገኝ እርዳታ እና ስጦታ፣
- ከብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የሚገኝ ድጋፍ፣
- በፌደራል መንግስት ወይም በብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድሮች ፈቃድ የሚሰበሰብ ገንዘብ፡፡

ምዕራፍ ሰባት፡ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 44፡ የፓርቲው የምርጫና የድምጽ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

1. ማንኛውም የፓርቲው ስብሰባ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤው እንደተሟላ ይቆጠራል፣
2. በፓርቲው ውስጥ በማናቸውም ደረጃ ለሚወሰን ውሳኔ አንድ አባል አንድ ድምጽ ብቻ ይኖረዋል፣
3. በፓርቲው የተለያየ እርከን ምርጫ ሲካሄድ በቅድሚያ አስመራጭ ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ብዛት በብሄራዊ ደረጃ 5 (አምስት) ከዚያ በታች ባሉ እርከኖች 3 (ሶስት) ይሆናል፣
4. የፓርቲው አመራር አካላት ምርጫ በሚስጥር የድምጽ አሰጣጥ ስርአት ይካሄዳል፡፡
5. መተዳደሪያ ደንብን ከማሻሻል እና ፓርቲውን ከማፍረስ ጋር የተያያዙ ውሳኔዎች ውጪ ሌሎች ውሳኔዎች የሚያልፉት በስብሰባው ከተገኙ ከግማሽ በላይ በሚሆኑ አባላት ሲደገፉ ነው፣
6. በፓርቲው የጠቅላላ ጉባኤ፣ የክልል እና የወረዳ ሸንጎ ስብሰባዎች ላይ ተጋባዥ እንግዶች ሊጠሩ ይችላሉ፡፡ ተጋባዥ እንግዶች በማንኛውም ውሳኔ ላይ ድምጽ አይሰጡም፣

አንቀጽ 45፡ ስለ ደንብ ማሻሻል እና በደንቡ ውስጥ ስላልተካተቱ ጉዳዮች

1. የመተዳደሪያ ደንቡን ለማሻሻል ከጠቅላላ ጉባኤ አባላት ቢያንስ 1/3ኛ የሚሆኑ ጥያቄ ሲያቀርቡ እና የማሻሻያ ጥያቄው ከጠቅላላ ጉባኤው አባላት በ2/3ኛ ድምጽ ሲወሰን ነው፣
2. በፓርቲው እንቅስቃሴ ወቅት በዚህ ደንብ በግልጽ ያልተካተቱ ጉዳዮች ቢያጋጥሙና በፓርቲው አሰራር ላይ የስራ መስተጓጎል ቢያጋጥም የፓርቲው ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ግዚያዊ ውሳኔ በመስጠት ስራዎች እንዲሰሩ የሚያደርግ ሲሆን፣ ጉዳዩ ቋሚ መፍትሄ እንዲያገኝ እንደ አስፈላጊነቱ ለፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ወይም ጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ህግ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

አንቀጽ 46፡ ስለፓርቲ መፍረስ

ፓርቲው ሊፈርስ የሚችለው የመፍረስ ጥያቄው ከጠቅላላ ጉባኤ አባላት ቢያንስ 1/2 ጥያቄ ሲያቀርቡ እና ከጠቅላላ ጉባኤ አባላት በ 2/3ኛ ድምጽ ድጋፍ ሲያገኝ ብቻ ነው፡፡

አንቀጽ 47፡ ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ጠቅላላ ጉባኤ ከፀደቀበት ከመጋቢት 15፣ 2015 ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡